# የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ

**ዝናሽ ሰለሞን**

**ዘሪሁን አስፋው (ተ/ፐ)**

**የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)**

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሀድያ ብሔረሰብ አባላት በባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጽሟቸውን ክዋኔዎች ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ያላቸውን ትርጉም መግለጽና መተንተን ነው። በተጨማሪም በመተጫጨት ሂደት የሽማግሌዎችን ሚና ማሳየት እና በሠርግ ሥነ ሥርዓቱ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን ይዘት መተንተን ንዑሳን ዓላማዎቹ ናቸው። ጥናቱን ለማድረግ መነሻ የሆነኝ የመጀመሪያው ምክንያት ቢጋብቻ ክዋኔው ላይ የሚታዩ ድርጊቶችና ተከታታይ ሁነቶች ፎክሎራዊ ገጽታ እንዳላቸው በተለያየ አጋጣሚ ማየቴ ሲሆን ጥናት በማድረግም እያንዳንዱ ክዋኔ ለምንና እንዴት እንደሚከወን በጥልቀት ለማወቅ ማሰቤ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ቢጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት የሚታዩ ባህላዊ ገጽታዎች ከጊዜ ወደጊዜ በዘመናዊው እየተተኩ በመምጣታቸው ሙሉ በሙሉ ከመጥፋታቸው በፊት አሁን ያሉትን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ መረጃዎች በመሰብሰብ ተንትኖ ማቅረብና ሰንዶ ማስቀመጡ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። በጥናቱም የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ እንዴት ይከናወናል? በየክዋኔው ውስጥ ያለው ትርጉምስ ምንድን ነው? በሠርግ ወቅት የሚዘፈኑ ዘፈኖች ይዘት ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል። ጥናቱ አይነታዊ (Qualitative) ሲሆን የጥናቱን አላማ ለማሳካት በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች በ2012 ዓ/ም ከነበሩ ባህላዊ ጋብቻዎች በሦስት ሠርግ፣ በሁለት መልስና በአንድ የጋብቻ ጥየቃ ሥነ ሥርዓት ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ በመገኘት በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ክዋኔና ዐውድን መሰረት ባደረገ ዘዴ ገለጻና ትንተና ተደርጎባቸዋል። ከመረጃ ትንተናው ለመረዳት እንደተቻለው በሀድያ ብሔረሰብ ዘንድ የሚታወቁ አራት የጋብቻ ዓይነቶች ሲኖሩ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸመው (ለዲሻ) የጋብቻ ዓይነት መሆኑን ነው። በዚህ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከመተጫጨት እስከ ቅልቅል በሚፈጽሟቸው ክዋኔዎች አማካይነት የብሔረሰቡ አባላት እራሳቸውን እንደሚገልጹ በጥናቱ ታይቷል። የጥናቱ ግኝት የሚያመለክተው በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚለበሱ አልባሳት፣ የሚበሉ ባህላዊ ምግቦችና የሚጠጡ መጠጦች እንዲሁም የሚዘፈኑ ዘፈኖች እየተከናወነ ያለውን ሂደት የሚጠቁሙ እንጂ እንዲሁ የሚዘጋጁ አለመሆናቸውን ነው። በእያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ አማካይነት የሚተላለፉ መልዕክቶችም ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙና ብሔረሰቡን የመግለጽ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

ቁልፍ ቃላት:- [ሥነ ሥርዓት፣ ክዋኔ፣ ዐውድ]

## 1. መግቢያ

የሥነ ሥርዓትን (Ritual) ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ይሰጣሉ። ከነዚህ መካከል ሥነ ሥርዓት ማህበራዊ ልማድን፣ ታሪካዊ ተግባራትን እና በየዕለቱ የሚደጋገሙ Bell (1997፡171) ክንውኖችን የሚያካትት እንደሆነ ያስረዳሉ። Sims and Stephens (2005፡95) ደግሞ ሥነ ሥርዓት እንደ አንድ ማህበረሰባዊ የልማድ ዓይነት የሚታይና በተለያዩ የፎክሎር ምሁራን ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶት እየተጠና ያለ መሆኑን ይገልጻሉ። Mazama and Asante (2009፡575) በበኩላቸው ሥነ ሥርዓት መንፈሳዊ/ዓለማዊ ድርጊቶች የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የሚገልጽ ሲሆን በማህበረሰቡ በሚሰጠው እውቅና መሠረት ሁልጊዜ በማክበር በድግግሞሽ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር ነው።

ምሁራኑ ከሰጡት ብያኔ በመነሳት ሥነ ሥርዓቶች የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት ከወትሮው ለየት የሚሉ ማህበራዊ ክስተትና አጋጣሚን ለማብሰር የሚዘጋጁ ናቸው ማለት ይቻላል። እንዲሁም ተደጋግመው በመከወናቸው የማህበረሰቡን ባህርይ የሚያመለክቱ ክንውኖች ስብስብ ይሆናሉ።

Bell (1997፡94) የሥነ ሥርዓት ዓይነቶችን የሕይወት ዘመን ሽግግር (rites of passage)፣ ዓመታዊ (calendrical rites)፣ የልውውጥና መስዋዕት ማቅረቢያ (rites of exchange and communion)፣ ከበሽታ ለመፈወስ የሚፈጸሙ (rites of affliction)፣ ጾምና ግብዣን ተከትለው የሚመጡ (rites of feasting,fasting and festivals) እና ፖለቲካዊ (Poltical rites) በማለት በስድስት ይከፍሉታል።

ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩ ስድስት የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች አንዱ በሆነው የሕይወት ዘመን ሽግግር ውስጥ በሚካተተው ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ይሆናል።

የጥናቱ ዋና ዓላማ የሀድያ ብሔረሰብ አባላት በባህላዊው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጽሟቸውን ክዋኔዎች ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ያላቸውን ትርጉምና ፋይዳ መግለጽና መተንተን ሲሆን በመተጫጨት ሂደት የሽማግሌዎችን ሚና ማሳየት እና በሠርግ ሥነ ሥርዓቱ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን ይዘት መተንተን ንዑሳን ዓላማዎቹ ናቸው።

በጥናቱም ከሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓት አንዱ የሆነው  የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ እንዴት ይከናወናል? በየክዋኔው ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ትርጉም ምንድን ነው? በሠርግ ወቅት የሚዘፈኑ ዘፈኖች ይዘት ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል።

ጥናቱ በርዕሰ ጉዳይና በቦታ የተወሰነ ነው። ርዕሰ ጉዳይን በተመለከተ ከሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓቶች አንዱ በሆነው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ላይ ሲሆን በሥነ ሥርዓቱ አከዋወን ወቅት ጎልተው የሚወጡ ድርጊቶችን፣ የሚገለገሉባቸውን ቁሶችና ሥነ ቃሎች መግለጽና መተንተን ላይ ያተኩራል። በመሆኑም ጥናቱ ሌሎቹን የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓቶች አይመለከትም። ቦታን በተመለከተ በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች ማለትም ምስራቅና ምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳዎች ላይ

ይሆናል። ወረዳዎቹ ከዞኑ ዋና ከተማ ሆሳዕና ዘጠና ስድስት ኪሎሜትር ተገንጥለው በሾኔ አካባቢ ይገኛሉ።

### 1.1 የሀድያ ብሔረሰብ አካባቢያዊ ዳራ

ሀድያ ዞን በደቡብ ክልል ከሚገኙ አስራ አራት ዞኖች አንዱ ሲሆን ዞኑ በአስር ወረዳዎችና በአንድ የከተማ አስተዳደር እንዲሁም በ 323 የገጠር ቀበሌዎች የተደራጀ ነው። የዞኑ ዋና ከተማ ሆሳዕና ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ 205 ኪሎሜትር ላይ ይገኛል። ሀድያ ዞንን የተለያዩ ወረዳዎችና ልዩ ወረዳዎች ያዋስኑታል። እነሱም በስተሰሜን ጉራጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ስልጤ፣ በደቡብ ወላይታ፣ በምስራቅ ከንባታ፣ በምዕራብ ጊቤ ወንዝና የም ልዩ ወረዳ ናቸው (Solomon.2008:1-3)። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የባዳዋቾ ወረዳ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ በ345 ኪ.ሜ፣ ከክልሉ ሀዋሳ በስተምዕራብ 120 ኪ.ሜ እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ሆሳዕና 96 ኪ.ሜ እርቀት ላይ ይገኛል።

በሀድያ አካባቢ የብሔረሰቡን አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳዩ የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች አሉ። ከነዚህ መካከል የማህበረሰቡን ማህበረባህላዊ ሕይወት የሚያመለክቱትን እና ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመዱትን የብሔረሰቡን ባህላዊ የአስተዳደር ተቋምና ከብት የማስቆጠር ሥነ ሥርዓትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

የሀድያ ብሔረሰብ አምስት ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት አሉት። እነሱም ሚኔ፣ ነፈራ፣ ሞሎ፣ ሶሎ እና ጊራ ናቸው። “ሚኔ” በጣም ጥቃቅን የማህበረሰቡን ጉዳዮች በሀላፊነት የሚከታተል ሲሆን አባላቱም ውስን ናቸው። “ነፈራ” ሁለተኛው የስልጣን እርከን ሲሆን የዚህ ስልጣን አባላት የሠርግ ሥነ ሥርዓት ባለበት አካባቢ በመገኘት ከእንጨት መፍለጥ እስከመስተንግዶ ያለውን ሥራ ያከናውናሉ። “ሞሎ” ከሌሎቹ የስልጣን እርከኖች አልፈው የሚመጡ ጉዳዮችን የማየትና ውሳኔ የመስጠት ሚና አላቸው። “ሱሎ” እንደ አንድ የሀድያ ተቋም በሀድያ ውስጥ የዝምድናን ጋብቻ የመከላከል ሀላፊነት አለባቸው። በሀድያ ባህል መሠረት በአባትም ሆነ በእናት እስከሰባት ቤት በሚጋሩ ግለሰቦች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጸም ቁጥጥር ያደርጋሉ። በመጨረሻ የምናገኘው አጠቃላዩን የሀድያን ህዝብ የሚያቅፈው ትልቁ መዋቅር “ጊራ” የሚባለው ሲሆን ጦርነትን፣ የግብር ሙብዛትን የመቃወምና የህዝቡን ሙብት የማስፈጸም ስልጣን እንዳለው ይነገራል (አለባቸው እና ሳሙኤል። 2002፣141-153)።

አንድ ግለሰብ ከላይ ባየናቸው ባህላዊ ተቋማት ለመሾምና ለመመረጥ በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን የተለያዩ ጉዳዮች በጥንቃቄ የመመርመር ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር የመተንበይና ማህበረሰቡን የማስጠንቀቅ ብቃት እንዳለው የተመሰከረለት ሊሆን ይገባል።

በሀድያ ብሔረሰብ ባህል መሰረት የበርካታ ከብት ባለቤት መሆን ማህበራዊ ከበሬታን ያሰጣል። በመሆኑም ከአንድ መቶ እስከ አስር ሺ የማስቆጠር ወይም የማስመረቅ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። ከብት የማስመረቁ ሥነ ሥርዓት የሚከናወነው ዘመድ አዝማድ በተገኘበት በአካባቢው በሚገኝ ወንዝ አጠገብ ሲሆን እንደከብቶቹ ብዛት አስቆጣሪው የክብር ማዕረግ ይሰጠዋል፤ባለብዙ ከብት ባለቤት በመሆኑም ይከበራል።

በሀድያ ባህል የአንድ ግለሰብ የከብት ብዛት የሚነገረው እያንዳንዱን ከብት በመቁጠር ያለውን ሙሉ ቁጥር ሳይሆን የተለያየ ብዛት ያላቸውን የከብት ስብስቦች ታሳቢ በማድረግ የከብት ብዛትን የሚወክል አራት የተለያየ መጠሪያዎችን በመጠቀም ነው። በመሆኑም አንድ ግለሰብ እስከ 20 ከብት ሲኖረው "ፎርገሳ" እስከ 80 ከብት ሲያረባ የግለሰቡ የከብቶች ብዛት በጥቅሉ "ጉበንታ" ተብሎ ይጠራል። አንድ ግለሰብ እስከ 100 የሚደርሱ ከብቶችን ካረባ በጥቅሉ "ጥቤ" የሚል መጠሪያ ይሰጣቸዋል። እስከ 1000 ለሚደርሱ ከብቶች አንድ ግለሰብ ባለቤት ከሆነ በጥቅሉ "ኩማ" ተብሎ ይጠራል (አለባቸውና ሳሙኤል። 2002፣124)።

አንድ ግለሰብ የከብት ቆጠራ ሥነ ሥርዓት ከተካሄደለት በኢኮኖሚ የተሻለ ከመሆኑ በላይ በባህሉ መሰረት ለተግባሩ የተለየ ባህላዊ የማዕረግ ስያሜና ሹመት ይሰጠዋል። ማዕረጉ የተሰጠው ከብት አርቢም ማህበራዊ ደረጃው ከፍ የሚል ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድም የተለየ ክብርና ዝና ይሰጠዋል።

በአጠቃላይ የሀድያ ብሔረሰብ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ባህላዊ እሴቶቹ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ጥናትም ሌላኛው የማህበረሰቡን ማንነት ማሳያ የሆነው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ሂደት አጠቃላይ ገጽታ ምን እንደሚመስል ተዳሷል።

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ተነስተዋል። የመጀመሪያው የጥናቱን ጽንሰ ሀሳቦች የያዘ ሲሆን ሁለተኛው የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ ነው።

### 2.1 የፅንሰ ሀሳብ መሠረቶች

ከጥናቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጽንሰ ሀሳቦች ማለትም የሥነ ሥርዓት ምንነት፣ የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች፣ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሥነ ሥርዓትና የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ምንነት ተብራርቷል።

#### 2.1.1 ሥነ ሥርዓት (Ritual)

የሥነ ሥርዓትን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ይሰጣሉ። ከነዚህ መካከል Gennep (1960፡2-3) ሥነ ሥርዓት አንድ ግለሰብ ከአንዱ የዕድሜ ደረጃ ወደሌላ የዕድሜ ደረጃ መሸጋገሩን ምክንያት በማድረግ የሚያከብረው መሆኑን ያስረዳሉ። Bell (1997፡171) ሥነ ሥርዓቶች የሚደጋገሙ፣ ቅደም ተከተል ያላቸው፣ ተከታታይ ትዕምርቶችንና ድርጊቶችን ያካተቱ ክዋኔዎች ናቸው በማለት ይገልጻሉ። Dorson (1972፡159) ደግሞ ሥነ ሥርዓቶች በዋናነት ከአንድ ወቅት ወደሌላ ወቅት እንዲሁም ከአንድ የሕይወት ዑደት አበይት ክፍሎች ወደሌላው የምንሸጋገርበትን የሚያበስሩ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ሥነ ሥርዓት የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት በየደረጃው የሚገኙና ከወትሮው ለየት የሚሉ ማህበራዊ ክስተትና አጋጣሚን ለማብሰር የሚዘጋጅ ነው። ከነዚህ ማህበራዊ ክስተቶች መካከል የሕይወት ዘመን ሽግግር አበይት ክፍሎች ልደት፣ ግርዛት፣ ጉርምስና፣ ጋብቻ እንዲሁም ሞት በዋናነት የሚጠቀሱ ሥነ ሥርዓቶች ናቸው። እነዚህም የሽግግር ወቅቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነትን ያገኙና ለየት ያሉ የሕይወት አጋጣሚዎች ደማቅ በሆነ ሥነ ሥርዓት ይከበራሉ

"Rituals ferequentely signal important stage of life, rituals are associated with birth, puberity, marriage, and death and rituals establish our entry to or exit from different parts of life" (Sims and Stephens 2005:94) ፡፡

ከላይ የተገለጹ ብያኔዎችን መነሻ በማድረግ ሥነ ሥርዓቶች ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደሌላ ሽግግር ማድረግን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ክንውኖች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት ከሽግግር ሥነ ሥርዓት አንዱ የሆነውን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ክዋኔን መግለጽና መተርጎም ይሆናል፡፡

### 2.1.2 የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች

የሥነ ሥርዓት ዓይነቶችን Sims and Stephens (2005፡134) በሁለት የሚመድቡ ሲሆን እነዚህም የከፍተኛ ዐውድ ሥነ ሥርዓትና የዝቅተኛ ዐውድ ሥነ ሥርዓት ናቸው፡፡ Dorson (1972: 161) ደግሞ የሥነ ሥርዓት ዓይነቶችን በተ ያልተገደበ እና በተሳትፎ የተገደበ በማለት በሁለት ይመድቡታል፡፡ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ሳትፎ Bell (1997፡94) የሥነ ሥርዓት ዓይነቶችን የሕይወት ዘመን ሽግግር (rites of passage)፣ ዓመታዊ (calendrical rites)፣ የልውውጥና መስዋዕት ማቅረቢያ (rites of exchange and communion)፣ ከበሽታ ለመፈወስ የሚፈጸሙ (rites of affliction)፣ ጾምና ግብዣን ተከትለው የሚመጡ (rites of feasting, fasting and festivals) እና ፖለቲካዊ (Poltical rites) በማለት በስድስት ይመድቡታል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት ከነዚህ ስድስት የሥነ ሥርዓት ዓይነቶች መካከል በሕይወት ዘመን ሽግግር ውስጥ የሚካተተው ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡

#### የጋብቻ ሥነ ሥርዓት

ጋብቻ አንዱ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሲሆን በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚፈጠር ውህደትና አብሮ ለመኖር የሚደረግ ስምምነትን የሚያሳይ ነው፡፡ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንደማህበረሰቡ ባህልና የሕይወት ልምድ ከሚከበሩ ሥነ ሥርዓቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ ጋብቻ በተለያየ ሥነ ሥርዓት በድምቀት ይከበራል፡፡ ሥነ ሥርዓቱ ሲከበር እየተደረገ ያለውን የሕይወት ሽግግር የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ፡፡ እንዲሁም ከተለመደው ወጣ ያሉና በልዩ ትኩረት የተዘጋጁ ምግብና መጠጦች ይዘጋጁና ቀኑን በማይረሳ መልክ ያከብሩታል፡፡

በጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት በልዩ ትኩረት የሚዘጋጁ የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች፣ ሙሽራውና ሙሽሪት የሚለብሷቸው አልባሳት፣ በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚጨፈሩ ጭፈራዎች፣ የሠርግ ሥነ ሥርዓቱ የሚካሄድበት አደራሽ ውስጥ ውበትን ለመፍጠር ታስበው የሚሰቀሉ ጌጣ ጌጦችና ባጠቃላይ በጋብቻው ወቅት የሚከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶች እየተከናወነ ያለውን ማህበራዊ ሽግግር የሚጠቁሙ ናቸው "Numerous features of the ritual are special event markers oral performance; special foods, perhaps, foods requiring time consuming

preparation; dramatic lighting (dimlight), spot lights of some sort" (Sims and Stephens.2005: 97)።

በጋብቻ ላይ የሚከወኑ ሥነ ሥርዓቶች እንደማህበረሰቡ ባህል፣ እምነትና ልማድ የተለያዩ ቢሆኑም ሥነ ሥርዓቱ ህልውና ይኖረው ዘንድ መከወናቸው የግድ ነው። የሀድያ ብሔረሰብ አባላትም ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ ጋብቻን በተለያየ ሥነ ሥርዓት በድምቀት ያከብሩታል።

### 2.2 የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ እና ዐውድ ተኮር ሥነ ዘዴ ጥቅም ላይ ውለዋል። በንድፈ ሀሳቦቹ መሰረትነት የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ እንዴት እና በምን ዓይነት ዐውድ እንደሚከወንም ገለጻና ትንተና ተሰጥቶበታል።

#### 2.2.1 ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ

ክዋኔ ማለት በዋናነት እንደተግባቦት ባህርይ የሚታይ ሲሆን አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚፈጸሙ ኪናዊ ጉዳዮችን በሙሉ ያጠቃልላል። ክዋኔ በራሱ መንገድ ተቀምሮ ለታዳሚ የሚደርስ፣ የሚከናወነው ጉዳይ የሚታወቅበት እና ሰዎች በተግባቦት ሂደታቸው ውስጥ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው (Bauman.1992፡3)።

ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ፎክሎርን አገልግሎት በሚሰጥበት ማህበራዊ እና ባህላዊ ዐውድ ውስጥ አስገብቶ ለመተንተን ያስቻለ ነው። በመሆኑም የአንድን ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ምንነት ለመረዳት የሚከወንበትን አጠቃላይ ገጽታ ወይም የሚቀርብበትን ማህበራዊ ዐውድ መረዳት ተገቢ ነው።

ክዋኔ ምንጊዜም ከሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን ክዋኔው ከአጋጣሚ አጋጣሚ የተለያየ ነዉ። በክዋኔዉ የሚተላለፈው መልዕክትም በዚያው ልክ ይለያያል። በመሆኑም አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለማጥናት ማህበረሰቡ ተስማምቶ ያዋቀረው ደንብ መታወቅ አለበት። ክዋኔ ከዋኙን፣ ክዋኔው የሚካሄድበትን አጋጣሚ፣ የአከዋወን ስልቱን፣ ተሳታፊውን፣ በከዋኙና በተሳታፊዎቹ መካከል ያለውን መስተጋብር ያካትታል። ከዚህም በተጨማሪ አጋጣሚውን ያስገኘውን ማህበረሰብ ባህላዊ ዳራ ከግምት ውስጥ ያስገባል (Sims and Stephens.2005:149)።

የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎር ህልውና የሚኖረው ክዋኔ ሲኖር ብቻ ነው። የክዋኔው ሂደት ስፋትና ጥልቀትም በማህበረሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ባህላዊ ሁኔታዎች የሚወሰን ነው። በመሆኑም በጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ የሚከወነው እያንዳንዱ ተግባር ለባህሉ ባለቤቶች ያለው ትርጉም በትኩረት ሊታይና ሊተነተን ይገባል።

#### 2.2.2 ዐውድ ተኮር ስነ ዘዴ

ዐውድ በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ወቅት ያለዉን አጠቃላይ ሁነት ማለትም በክዋኔው ወቅት የሚከሰቱትን እያንዳንዱን ጥቃቅን ክስተቶች ሳይቀር የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው። በመሆኑም

የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ መልዕክት በወጉ ለመረዳት የዐውዱን አጠቃላይ ድባብ ማወቅና መተርጎም ይገባል። Ben Amos (1993፡210) እንደሚሉት የአንድ ፎክሎር ክዋኔ ሂደት ትርጉም የሚኖረዉ በዐውዱ እና ዐውዱ በሚሰጠዉ ትርጉም መሰረት ሲጠና ነው። በመሆኑም ስለእያንዳንዱ ክዋኔ ተግባር በወጉ ለመናገር ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያቀርብበትን ዐውድ ጠንቅቆ ማወቁ ተገቢ ነው።

የዐውድ አይነቶችን ምሁራን በተለያየ መንገድ ይከፋፍሉታል። ከነዚህ መካከል Sims and Stephens (2005፡138) ዐውድን "ተጨባጭ" ዐውድና "ማህበራዊ" ዐውድ በማለት በሁለት ይመድባሉ። የዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ አቀንቃኝ የሆኑት Bauman (1983፡363-367) ደግሞ ዐውድን "ማህበራዊ" እና "ባህላዊ" በማለት በሁለት ይከፍሉታል። ባህላዊ ዐውድ በውስጡ ልማዳዊ ተግባራትን እና የሰዎች አኗኗር በፎክሎሩ ውስጥ የተቀረጸበትን መንገድ ያሳያል፤ከዚህም በተጨማሪ እንደ ሃይማኖት፣ ዝምድና፣ ጉርብትና፣ ከበራ፣ ጸሎት ያሉ ማህበራዊ እሴቶችን ይመለከታል። ማህበራዊ ዐውድ ደግሞ ማህበራዊ መዋቅሮችንና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በውስጡ ይይዛል። እንዲሁም በከዋኙና በታዳሚው መካከል የሚኖረውን መስተጋብር ያጠቃልላል።

Ben Amos (1993:216) ደግሞ የዐውድ ዓይነቶችን ባህላዊ ዐውድ" እና "ሁኔታዊ ዐውድ" በማለት በሁለት መድበው ስለምንነታቸው ያስረዳሉ። ባህላዊ ዐውድ የሚባለው ሰፋ ያለና ሌሎች የዐውድ ዓይነቶችን በዉስጡ የሚያቅፍ ነው። ክዋኔው የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነውን ጉዳይ፣ የተሳታፊዎችን የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኞቹን እውቀትና የሥነ ምግባር ህጎች ያካትታል። ሁኔታዊ ዐውድ ደግሞ የሚከወነው ጉዳይ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን የአንድን ክዋኔ ተለምዷዊ አካሄድ ድንገት የሚቀይሩ ጉዳዮችንም ይመለከታል።

የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሰረተው በዚሁ Ben Amos ባስቀመጧቸው ባህላዊ ዐውድና ሁኔታዊ ዐውድ በሚለው ነው። ምክንያቱም በባህላዊ ዐውድ ስር ሰፊ የሆነውን የማህበረሰብ አስተሳሰብ እና ልማዳዊ ህግጋት መመልከት የሚቻል ሲሆን በሁኔታዊ ዐውድ ስር ደግሞ በክዋኔው ወቅት የሚከሰቱ ሁነቶችን እና በፎክሎራዊው ክዋኔ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መመርመር ስለሚያስችል በሁለቱ ዐውዶች ውስጥ ሌሎቹን መመልከት ይቻላል።

### 3. የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) ሲሆን የጥናቱን አላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችል ዘንድ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል። አንድ አጥኚ ወደ መስክ ከመሄዱ በፊት ለመስክ ሥራው መሰረት የሚሆን መረጃን በማግኘትና በማንበብ የመስክ ሥራውን አቅጣጫ ማስያዝ እንዳለበት Goldstein (1964፡37) ይገልጻሉ። በመሆኑም ካልኣይ መረጃን ለማሰባሰብ ስለአካባቢው የተጻፉ የተለያዩ ሰነዶች ፍተሻ ተደርጎባቸዋል። ሰነዶቹ የተገኙት ከክልል፣ ከዞንና ወረዳ መንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮዎች ውስጥ ነው። ቀዳማይ መረጃዎች ደግሞ ከመስክ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኙ ጥሬ መረጃዎች ናቸው።

ለፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች መካከከል ዋናውና ቀዳሚው ምልከታ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው የፎክሎር ጥናት ከመስክ በሚሰበሰብ ተፈጥሮአዊ ዐውድ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የሚፈልግና ምልከታ የግድ የሚሆንበት አጋጣሚው ብዙ ነው። ምልከታ በዓይን ብቻ የሚታይ ሳይሆን ከሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን ጋር ህብረት በመፍጠር የተሟላ መረጃ የሚገኝበት ዓይነተኛ ስልት ነው (Goldstein .1964:77)።

በመሆኑም ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች በ2012 ዓ.ም ከነበሩ ባህላዊ ሠርጎች በሦስት ሠርግ፣ በአንድ መልስና በአንድ የጋብቻ ጥየቃ ሥነ ሥርዓት ተፈጥሮአዊ ዐውድ ላይ በመገኘት በምልከታና የጥናቱን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉ ሀያ የመረጃ ሰጪዎችን በቃለ መጠይቅ በማሳተፍ ነው። ከነዚህ መካከል አስሩ ወንዶች ሲሆኑ አስሩ ደግሞ ሴቶች ናቸው።

መረጃዎች በአብዛኛው የተሰበሰቡት ከሀድይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመሆኑ ለሥራው ያመች ዘንድ ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል። ለትርጎማው የተመረጡት ከዚህ በፊት በአካባቢው የሚሰሩ መጽሐፎች ላይ በትርጉም ይሳተፉ የነበሩት አቶ መንገሻ ኀቤቦ ሲሆኑ የሀድይኛውን ፍቺ ቃል በቃልና ዐውዳዊ ትርጉሙን በመተርጎም ተሳትፈዋል። አጥኚው የቋንቋው ተናጋሪ በመሆኑ አንዳንድ ቃለ መጠይቆችን ለመተርጎም ባይቸገርም በተሻለ ቋንቋውን በሚችሉ ሰዎች ትክክለኛነቱን ለማስገምገም ጥረት አድርጓል። በመጨረሻም የሀድይኛውን ፍቺ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ስሜት መስጠት አለመስጠቱን በማየት ስሜት የማይሰጠው ተለይቶ ማሻሻያ ተደርጎበታል።

በቀጣዩ ክፍል ከመስክ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት አጠቃላይ ሂደት ምን እንደሚመስል ተተንትኖ ቀርቧል።

### 4. ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከዋኔ ዐውዳዊ ትንተና

ጋብቻ አንዱ የሕይወት ዘመን ሽግግር ሲሆን በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጠር ውህደትና አብሮ ለመኖር የሚደረግ ስምምነትን የሚያሳይ ነው። ሰዎች አቅማቸውና የሚኖሩበት አካባቢ ባህልና ወግ እንደሚፈቅደው ጋብቻን በተለያየ ሥነ ሥርዓት ያከብሩታል። የማህበረሰቡ አባላት በተለያየ የሕይወት ዕድገት ደረጃዎች አልፈው ማህበረሰቡ ከፍተኛ ትኩረት ወደሚሰጠው የትዳር ሀላፊነት የሚሸጋገሩበት ልዩ ቀን በመሆኑ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። ሥነ ሥርዓቱ ሲከበርም እየተደረገ ያለውን የሕይወት ሽግግር የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሥነ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ። ከተለመደው ወጣ ያሉና በልዩ ትኩረት የተዘጋጁ ምግብና መጠጦች ይዘጋጁና ቀኑን በማይረሳ መልክ ያከብሩታል።

ጋብቻ የሚመሰረተው በዋናነት ትውልድን ወደፊት ለማስቀጠል በመሆኑ በታላቅ ደስታ ይከበራል። ወላጆች ልጆቻቸው ለጋብቻ ወግ ማዕረግ ሲደርሱላቸው ከመደሰታቸው የተነሳ አቅማቸው በሚፈቅደው ሁኔታ ድግስ ደግሰው ዘመድ አዝማድ ጠርተው ቀኑን በማይረሳ መልኩ ያሳልፉታል። በአካባቢው ባህል መሠረት ሠርግ ተጠርቶ መቅረት ወዳጅነትን የሚያጠፋ በመሆኑ የተጠራ ሰው ሁሉ ወደ ሠርጉ ቤት በመሄድ የደስታው ተካፋይ ይሆናል።

### 4.1 የጋብቻ ዓይነቶች

በባዳዋቾ ሀድዮች ዘንድ የሚታወቁ የጋብቻ ዓይነቶች አራት ናቸው። እነሱም በቤተሰብ ስምምነት የሚከናወን (ለዲሻ)፣ ወዶ መግባት (ሄረንቻ)፣ ጠለፋ (ጎሰኖ)፣ እና የውርስ (ለጎ ) ጋብቻ ናቸው። እያንዳንዱ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የተለያየ አፈጻጸም ያለው ሲሆን በዚህ ጥናት የቀረበው በብሔረሰቡ ዘንድ ህጋዊ ተብሎ የሚታሰበውና በስፋት የሚፈጸመው በቤተሰብ ስምምነት የሚከናወነው (ለዲሻ) የጋብቻ ዓይነት ነው።

#### 4.1.1 በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ (ለዲሻ)

ይህ የጋብቻ ዓይነት በሁለቱ ቤተሰቦችና ተጋቢዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚፈጸም ሲሆን በባዳዋቾ ሀድዮች አካባቢ ከሚከናወኑ ባህላዊ ጋብቻዎች ዋነኛውና ህጋዊ ተብሎ የሚታሰበው ነው።

በቤተሰብ ስምምነት የሚያገባ አግቢ የሚያገባትን ልጅ በሁለት መንገድ ሊመርጥ ይችላል። የመጀመሪያው የልጁ አባት በአካባቢው መልካም ስነ ምግባር አላት ተብሎ የተመሰከረላትን ሴት በዘመድ አዝማድ አጠያይቆ ካገኘ በኋላ ለትዳር የደረሰውን ልጁን ሄዶ እንዲያያትና መውደድ አለመውደዱን እንዲገልጽለት የሚያደርግበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አግቢው ልጅ እራሱ የወደዳትን ልጅና የማን ልጅ እንደሆነች ለአባቱ የሚያሳውቅበት መንገድ ነው። ምርጫው ከሁለቱ በየትኛውም ቢሆን ጋብቻው የሚካሄደው በሙሽራውና በሙሽሪት ቤተሰቦች ስምምነት መሠረት ነው።

በቤተሰብ ስምምነት የሚያገባ አግቢ ሆኖ የሚያገባት ልጅ በወላጆቹ የተመረጠችለት ከሆነ በወላጆቹ ጥቆማ መሠረት ወደተባለው አድራሻ አንድ ጓደኛውን ይዞ ይሄዳል። ከጓደኛው ጋር በሚሄድበት ጊዜ የሚያጨው (ወጣቷን የሚፈልገው) ልጅ የቱ እንደሆነ እንዲታወቅ በእጁ አለንጋ ይይዛል። አለንጋ የሚይዝበት አንዱ ምክንያት የትዳር ፈላጊውን ማንነት ለማሳወቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሀድያ ባህል መሠረት አንድ ሰው ካጠፋ የሚቀጣው በአለንጋ በመሆኑ "አለንጋዬ ቀድሟልና እኔ እያለሁ ልጃችሁን ለሌላ ብትድሩ ትቀጣላችሁ" የሚል መልዕክት ማስተላለፊያ ነው። ስለዚህ ቀድሞ አለንጋ ይዞ ወደቤት የገባውን ትተው ለሌላ ሰው ልጃቸውን ከዳሩ በባህሉ መሠረት የሚጣልባቸው ቅጣት ከፍተኛ መሆኑ ስለሚታወቅ ቀዳሚው እያለ ማንም ደፍሮ ልጁን ለሌላ ሰው ሊድር አይችልም ማለት ነው።

ወንዱ ልጅ የትዳር አጋሩ እንድትሆን በቤተሰቡ የተመረጠችለትን ልጅ ለማየት ወደ ልጅቷ ቤት የሚሄደው ብቻውን ሳይሆን አንድ የቅርብ ጓደኛውን አስከትሎ ቢሆንም ይዞት የሚሄደው ጓደኛ ግን በመልክ ከሱ ሙብለጥ የለበትም። ምክንያቱም በመጀመሪያ እይታዋ በመልክ የተሻለውን ወንድ (ጓደኛውን) "ወድጄዋለሁ" ልትል ወይም ልትመርጥ ትችላለች። ከጓደኛው ጋር በመሆን ወደተመረጠችው ልጅ ቤት ሰፈር ይሄዱና እንደሚያልፍ ሰው በመሆን በር አካባቢ የሚያገኙትን ሰው ስለደከማቸው ትንሽ ማረፍ እንደሚፈልጉ በመናገር ወደ ቤት ይገቡና ቁጭ ይላሉ። ትንሽ እንደተቀመጡም የሚፈልጓትን ልጅ በደንብ ለማየት ያስችላቸው ዘንድ የተለያየ ትዕዛዝ እያዘዙ

ያመላልሷታል። በዚህ ምልልስ ወቅት ወደዚያ ወደዚህ ስትል አረማመዷን፣ የፊቷን ገጽታዋንና የሚፈልጉትን የማየት እድል ይኖራቸዋል ማለት ነው።

አግቢው ልጅ እራሱ በሚመርጥበት ጊዜ የሚፈልጋትን ልጅ በሠርግ፣ በገበያ፣ ወንዝ ውሃ ስትቀዳ ወይም ስንደዶ (ሚግራ) ለቀማ ቦታ ካያትና ከወደዳት ከኋላዋ ተከትሎ የምትገባበትን ቤትና የማን ልጅ እንደሆነች አጣርቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ሦስት አራት ቀን ልጅቷን እየተከታተለ ሲያያት ልጅቷ ለሱ ያላትን ፍላጎትና አመለካከት ማጣራትና ማረጋገጥ ይኖርበታል።

አስቀድመው ሁለቱ ጥንዶች ከተዋደዱና ለጋብቻ ከተስማሙ በባህሉ መሠረት ሽማግሌ እንዲላከለት ወንዱ ልጅ ለአባቱ የወደዳትን ልጅ ማንነት ያሳውቃል። ሴቷም አስቀድማ የልጁን ማንነት ለወላጆችዋ በመንገር ሽማግሌ የሚመጣበትን ቀን ታሳውቃለች። የልጁ አባት በልጁ ምርጫ ከተስማማ ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ጋ የሚሄዱ ሽማግሌዎችን ያዘጋጅና ቀጠሮ ይይዛል "የወንዱ ቤተሰቦች ወደ ሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ለመላክ የሚመርጧቸው ሽማግሌዎች ዝምድና መኖር አለመኖሩን፣ የቤተሰቡን ደረጃ፣ የእምነት ሁኔታ መመሳሰል አለመመሳሰሉን ሊያረጋግጡ የሚችሉ እንዲሁም በአካባቢው ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸው ሽማግሌዎች መሆን አለባቸው።" በሀድያ ባህል መሰረት ሽምግልና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ሲሆን በሽማግሌ የማይፈታ ምንም ጉዳይ አይኖርም። በመሆኑም በሁለቱ ቤተሰብ መካከል በመሆን እስከሠርጉ ማብቂያ ድረስ ያለውን አስፈላጊ ጉዳይ እንዲያስተካክሉ ሀላፊነት የሚሰጠው ለሚመረጡ ሽማግሌዎች ነው።

### 4.1.2 በቅድመ ጋብቻ የሚከወን ሥነ ሥርዓት

በባዳዋቾ ሀድዮች አካባቢ ህጋዊ ተብሎ የሚታሰበው የለዲሻ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከመፈጸሙ አስቀድሞ የሚከናወኑ በርካታ ሥነ ሥርዓቶች አሉ። ወንዱ ልጅ የትዳር አጋሩን እራሱ መርጦም ይሁን በወላጆቹ ተመርጦለት በባህሉ መሠረት የሚፈጸሙ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይጠበቅበታል። በመሆኑም አጥኚው በተመለከተው ሦስት ጋብቻ ወንዱ ልጅ የሚያገባትን ሴት መርጦና ተስማምቶ በቤተሰቡ በኩል "ልጃችሁን ለልጃችን" በማለት የመጀመሪያ ሽምግልና ከሚላክበት ዕለት ጀምሮ የነበረው ሥነ ሥርዓት ከዚህ በታች ተተንትኖ ቀርቧል።

#### 4.1.2.1 መተጫጨት (ጤሀቃንቻ)

በአብዛኛው የሀድያ ወጣቶች የመተጫጫ ዐውድ እንደሆነ የሚነገረው የስንደዶ ለቀማ (የሚግራ) ቦታ ነው። ለስንደዶ ለቀማ የሚወጡ ሴቶች ለጋብቻ የደረሱ ወጣቶች (ባጃም ለንዲቾ) በመሆናቸው አምረውና ተውበው የተለያዩ ዜማዎችን እያዜሙ የወደፊት የትዳር አጋራቸውን ለመምረጥ ወደቦታው ይሄዳሉ። የሀድያ ሴቶች ለስንደዶ ለቀማ ሲወጡ ከውበታቸው ባሻገር ወደፊት ትዳር ሲይዙ እራሳቸውን ችለው የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን መስራት መቻላቸውንና ሙያ እንዳላቸው ለወንዶቹ የሚያሳዩበት የተለየ ቀናቸው ነው።

የስንደዶ ለቀማ ዐውድ ወጣቶች እርስ በእርሳቸው እንዲግባቡና የአንድነት ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ሴቶቹና ወንዶቹ ፍቅራቸውን የሚገላለጹበትና የሚደናነቁበት እንደመሆኑ ከወንዶቹ መሀል አንዱ በስንደዶው ለቀማው ቦታ የወደዳትና ለትዳር የተመኛት ሴት ካለች እንደወደዳት ለማሳወቅ ከስንደዶው መሀል ረዘም ያለውን መርጦ ይሰጣታል። ይህ

የሚያመለክተው የተመረጠችው ልጅ ቆንጆና ረዘም ያለች መሆኗንና በዙሪያዋ ካሉ ሴቶች እሷ ብቻ መመረጧን ነው። ይህ አንዱና የመጀመሪያው የፍቅር መግለጫ መንገድ ሲሆን "እሷ የምትወደው ከሆነና በሀሳቡ የምትስማማ ከሆነ የሰጣትን ስንደዶ ትቀበለዋለች፤ካልፈለገችውና በሀሳቡ የማትስማማ ከሆነ ግን ስንደዶውን አትቀበለውም ይህ ቦታ አብዛኞቹ የሀድያ ሴቶች የትዳር አጋራቸውን ያገኙበት ቦታ እንደሆነ ይነገራል።" አሁን ባለው ሁኔታ ግን የዚህ ዓይነቱ ዐውድ እንደማይታይ አቶ ዘኪዎስ ሠጋሮ ይናገራሉ።

በባህሉ መሠረት ለጋብቻ ቀድሞ የሚጠይቀው ወንዱ ነው። የሚወዳትን ልጅ ለመምረጥ መስፈርት ሆኖ የሚያገለግለው ደግሞ አካላዊ ውበቷ፣ የባህላዊ ዘፈን ክህሎቷ እና በእድሜ እቻ መሆኗ ነው። ሴቷም ስምምነቷን የምትገልጸው በተመሳሳይ በአቋሙ፣ በፀባዩና በጭፈራው ከተማረከች ብቻ ነው።

#### 4.1.2.2 በመተጫጨት ሂደት የብሔረሰቡ የሽማግሌዎች ሚና

ሁለቱ ተጋቢዎች ከተስማሙ በኋላ በቤተሰብና በተመረጡ ሽማግሌዎች አማካይነት የጋብቻው ቅድመ ሁኔታ ይጀመራል። በዚህ ሂደት የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ሚና ከፍተኛ ሲሆን ለዚህ ጉዳይ የሚመረጡ ሽማግሌዎች በብሔረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፤ሰዎችን ማሳመን የሚችሉና ሊመጣ የሚችለውን ሀላፊነት በሙሉ የሚሸከሙ መሆን አለባቸው። ማለትም ሁለቱ ተጋቢዎች በትዳር ቆይታቸው አንዳች መጥፎ ነገር ቢደርስባቸው ሀላፊነትን መውሰድ የሚችሉና በሁለቱ ቤተሰብ መካከል የመሀል ሰው ሆነው እያንዳንዱን ጉዳይ የሚያስፈጽሙ ሰዎች መሆን አለባቸው።

ለጋብቻ ጥየቃ የተመረጡ ሽማግሌዎች ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ከመሄዳቸው በፊት ጋብቻው ስኬታማ መሆን አለመሆኑንና ኮከብ መግጠሙን (ጭኢች ኤደንቻ) በተለያዩ አጋጣሚዎች ማየት ይጀምራሉ። ለሽምግልና ወደ ሴት ቤተሰብ በሚኬድበት ቀን እግርን እንቅፋት ከመታ፣ ጦጣ፣ ሚዳቋና ባዶ እንስራ የተሸከመች ሴት ከፊት ከወጣች ነገሩ አይሰካም። ስለዚህ ሽምግልናውን ትቶ ወደቤት መመለስ ያስፈልጋል። በመንገድ በእንስራ ሙሉ ውሃ የተሸከመች ሴት ካጋጠመች፣ መንገድ ላይ ወንድ ካጋጠመና የጠፋ እሳት ሽማግሌዎች ቦታው ላይ ሲደርሱ በድንገት ከነደደ ኮከብ ገጥሟል ማለት ነው። ስለዚህ በሚሄዱበት ጥሩ ምላሽ ይዘው እንደሚመጡ በማመን ይሄዳሉ።

የመረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ትርጉም አለ "አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ጉዞ ተጀምሮ እግርን እንቅፋት ከመታ ጉዳዩ አይሳካም። ጦጣ እና ሚዳቋ መጥፎ እድል አመላካች ናቸው። ባዶ እንስራም ወደፊት የሚገጥመው ነገር ተስፋ እንደሌለው ማሳያ ነው።"

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በሁለቱ ቤተሰብ የሚፈጠረው የጋብቻ ዝምድና መልካም መሆን አለመሆኑን በባህሉ መሠረት የሚያረጋግጡበት ሌላ ዘዴም አላቸው። አንድ ወጣት የሚያገባትን ሴት እንዲያጭለት ለአባቱ ሲያሳወቅ አባት ምርጫው ልክ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ መልካም ዜና አብሳሪ ናት በመባል የምትታወቀው ወፍ መጮህ አለመጮህ ያረጋግጣል። እንደነገሩኝ ወፏ "ሲምብሬ" በመባል የምትታወቅ ሲሆን ጉዳዩ በታሰበ ሰሞን በቀኝ በኩል ስትጮህ ከተሰማ ጋብቻው

መልካም እንደሆነ በግራ በኩል ከጮኸች ግን ጋብቻው እንደማይሰምር ይታመናል “በሀድያ ብሔረሰብ እምነት ቀኝ የስኬት የመልካም ነገር ተምሳሌት ሲሆን ግራ የመጥፎ ነገር መገለጫ ነው። ” እንዲሁም የትጭጭት ሥነ ሥርዓቱ ተጀምሮ ሳለ ካለችበት ዛፍ ወረድ ብላ ስትጮህ ከታየች የትጭጭቱ ሥነ ሥርዓት ቶሎ እንደሚያልቅ ይታወቃል፤እራቅ ብላ ከጮኸች ደግሞ ጉዳዩ ቀጠሮ ይበዛበታል ወይም ቶሎ አይሳካም። ስለዚህ የወፏን ድምጽ ለመስማት በጉጉት ይጠበቃል።

በባዳዋቾ ሀድዮች አካባቢ ሴት ልጅ ለጋብቻ ለመጠየቅ ሴቷ ቤት የሄዱ ሽማግሌዎች ለምን እንደመጡ ሲጠየቁ “ወፍ (ምልኬ) መራችን” ብለው ይመልሳሉ። በመንገድ ላይ ሲሄዱም የሚታይ ማንኛውም ነገር ለጉዳዩ መሳካት ወይም አለመሳካት አንድ ምልክት ነው ብለው ያስባሉ “ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅ ለመጠየቅ (ለማጨት) ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ስንሄድ በእንስራ ሙሉ ውሃ የተሸከመች ሴት በመንገዳችን ካቋረጠች ልጁ የሚያገባት ሴት መልካም ገድ ይዛ ነው የምትመጣው ስለዚህ መንገድ ላይ የሚያጋጥመንን ነገር በሚገባ እንከታተላለን።”

ለጋብቻ ጥየቃ ሽማግሌዎች እንዲሄዱም ከሳምንቱ ቀናት ጥሩ ነገር ያስገኛሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ቀናት አሉ። እነዚህ ቀናት ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ ቅዳሜና እሁድ ሲሆኑ ሰኞ፣ እሮብና አርብ ለጋብቻ ጥየቃ የማይኬድባቸው ቀናት ናቸው “በድሮ ጊዜ በባዳዋቾ የሚኖሩ ሀድዮች ሰኞ፣ እሮብና አርብ ረሀብ፣ ጦርነት፣ የመሬት መንቀጥቀጥን የመሳሰሉ መጥፎ ነገር ተከስቶባቸው ስለነበር በነዚህ ቀናት ለጋብቻ ጥየቃ ብንሄድም መልካም ነገር አይገጥመንም ወይ መንገድ ላይ አንድ እንቅፋት ይፈጠርብናል።” በመሆኑም ሴት ልጅ ለመጠየቅ የሚሄዱት ከሳምንቱ ቀናት መካከል ጥሩ ነገርን ያመጣሉ ተብለው በሚታመንባቸው ቀናት ብቻ ነው። ሰኞ፣ እሮብና አርብ በፍጹም ተመራጭ ሊሆኑ አይችሉም።

ሽማግሌዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሄዱ ወደቤት የሚያስገባቸው ሰው ስለሚያዘጋጁ ያ ሰው ቀድሞ ገብቶ ወደ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ፈቃድ ጠይቆ እንዲመጣ ይላካል። የልጅቷ ቤተሰቦችም በተላከው ሰው አማካይነት “ፈቅደናልና ይግቡ” ብለው ምላሻቸውን ይሰጣሉ። ሽማግሌዎቹም ወደቤት ገብተው በተዘጋጀላቸው ቦታ ከመቀመጣቸው በፊት ቆመው “ቁጭ በሉ” እስኪባሉ ይጠባበቁና ሲፈቀድላቸው ይቀመጣሉ። ከተቀመጡም በኋላ ስለመጡበት ነገር ንግግር ከመጀመራቸው በፊት ዝም ብለው ለተወሰነ ደቂቃ ይቆያሉ። በእለቱ የተሰበሰቡ ሽማግሌዎች ለምን ጉዳይ እንደተሰበሰቡ ቢያውቁም የሴቷ ወገን ሽማግሌዎች “ለምን ጉዳይ መጣችሁ?” በማለት ይጠይቃሉ። እነሱም “ሰላም መሆናችሁን፣ ሀገር ሰላም መሆኑን ለመጠየቅ ነው የመጣነው” በማለት ምላሽ ይሰጣሉ። ወደ ዋናው የሽምግልና ጥየቃ በቀጥታ ስለማይገባ ሁሉም ተራ በተራ ከመጡበት ጉዳይ ጋር የማይገናኝ የተለያየ ነገር እያነሱ እየተጨዋወቱ ይቆያሉ። ከቆይታ በኋላም የወንዱ ሽማግሌዎች የመጣነው ከናንተ ልንዛመድ ነው (ኪኔንስ ቀረሜን ዋላሞ) ወይምሰው ፈልገን መጥተናል (መና ሀንሳሞ) ብለው ሀሳባቸውን ብዙም ግልጽ ባልሆነ የዳር ዳር በሆነ አይነት አጠያየቅ ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ።

ሽማግሌ ሲላክ በመጀመሪያ ዙር በምንም ዓይነት ሁኔታ አወንታዊ ምላሽ አይሰጥም። ስለሆነም በዕለቱ ለመጡ ሽማግሌዎች “እናንተ ሀሳባችሁን ነግራችሁናል እኛ ደግሞ እቤት ውስጥ ብዙ ሴቶች ስላሉ የትኛዋ እንደሆነች አጣርተን ከዘመድ አዝማድም ተመካክረን ምላሹን በሚቀጥለው ቀን

እናሳውቃለን" በማለት ለሳምንት ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ፡፡ በመጀመሪያ ቀን እሺ የማይባልበት ምክንያት "ከስምምነት በፊት መጣራት ያለባቸው ጉዳዮች ስለሚኖሩና ሽማግሌዎች ብዙ ተመላልሰው የተገኘች ሴት በባሏና በቤተሰቦቹ ዘንድ ስለምትከበር ማመላለሱ የግድ ነው፡፡" ስለዚህ ሁለተኛው ቀጠሮ እስከሚደርስበት ዕለት በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል ዝምድና እንዳይኖር የሚከለክል ነገር መኖር አለመኖሩ በጥንቃቄ መጣራት ይኖርበታል፡፡ ከነዚህ መካከል በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል በእናትና በአባት በኩል ያለ የቅርብ ዝምድና ይጠቀሳሉ፡፡ በሀድያ ባህል በእናትም ሆነ በአባት በኩል ተመሳሳይ ጎሳ ከሆኑ መጋባት አይፈቀድም፡፡ ማን የማንን ቤተሰብ ማግባት እንደሚችል በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በማጣራቱ ሂደት የጋብቻ ዝምድናውን የሚከለክል ነገር ካለ የትጭጭቱ ሥነ ሥርዓት እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ከሌለ ግን የሽምግልና ሂደቱ ይቀጥላል፡፡

### 4.1.2.3 የጥሎሽ (የገበራ) አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

የጥሎሽ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ሁለቱ ቤተሰቦች በጋብቻ ለመዛመድ ከተስማሙ ከአንድ ወር በኋላ ሽማግሌዎች ወደ አግቢዋ ቤት ሲመለሱ በልጅቷ ቤተሰቦች ዘንድ ከዚህ በፊት ከነበሩ ቀጠሮዎች በተለየ ሁኔታ በሬ/በግ ታርዶ ድግስ ተደግሶ ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤቶች እና የልጅቷ ወላጆች ተሰባስበው የእንግዶቹን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ ቀኑ ጥሎሽ የሚሰጥበት ብቻ ሳይሆን ወንዱ ልጅ ለሴቷ ቀለበት (ጉመአ) የሚያደርግበት ዕለት እንዲሁም የሠርጉ ቀን የሚቆረጥበት በመሆኑ በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡

የወንዱ ሽማግሌዎች ይዘው የመጡትን ጥሎሽ ለሴቷ ቤተሰቦች በዝምድናቸው ቅደም ተከተል በተራ በተራ የልብስና የገንዘብ ስጦታ ጉልበታቸው ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ጥሎሽ የደረሰው እያንዳንዱ ቤተሰብ በሠርጉ እለት ለሙሽራውና ለሙሽሪት ጎጆ መውጫ እንዲሆን የተለያዩ ዕቃዎችን በመግዛት እንደሚመለስ ስጦታ ሰጪዎችም ሆነ ተቀባዮቹ በሚገባ ያውቃሉ፡፡ በመሆኑም የወሰዱትን ጥሎሽ በእጥፍ ለሠርጉ ወይም ለመልሱ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

በጥሎሽ ዝርዝር ውስጥ የሚታዘዙ ነገሮች ከአቅም በላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢታወቅም አልችልም ወይም አላመጣም ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ጥሎሹን የሚያመጡት ቤተሰቦች ትልቅነታቸውን የሚያሳዩበት መንገድ እንደሆነ ስለሚያምኑ በመንደሩ ሰው ሁሉ እንዲከበሩ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ ያላቸውን ንብረት ሸጠውም ቢሆን የተባሉትን ወይም ከተባሉት ጋር የሚመጣጠን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከተባሉት ጋር የሚመጣጠን ነገር ለማምጣት ግን የቀጠሮ ቀን ከመድረሱ አስቀድመው ጉዳዩን ከያዙ ከሽማግሌዎቹ መካከል ሁለቱን በመላክ የማያመጡት ነገር መኖሩንና በምትኩ ይዘው የሚመጡትን ማሳወቅ አለባቸው፡፡

ጥሎሽ በሚቆጠርበት ዕለት ሊመጣ የማይችል ነገር እንዲያመጡ ማዘዝ የቤተሰቡን ትልቅነት ማሳያ ተደርጎ ይታሰባል "ሴት ልጅ ካገባች በኋላ በባሏ ቤተሰቦች የምትከበረው በባህሉ መሰረት በተገቢ ሁኔታ ጥሎሽ ተጥሎ ስታገባ ነው፡፡" በመሆኑም የቀጠሮው ቀን ሲወሰን የታዘዘውን ሁሉ ለሟሟላት በቂ መሆን አለበት፡፡ የሚባለውን ነገር ለማምጣት አቅም እንደማይኖርና እንደማይቻል እየታወቀም ከአቅም በላይ ነውና አላመጣም ማለት አይቻልም፡፡

በመቀጠል ሙሽራው ለሙሽሪት በቤተሰቦቿ ፊት ያመጣላትን ቀለበት እንዲያደርግላት ይደረጋል። ከቀለበቱ ሥነ ሥርዓት በኋላ በቤተሰብና በሽማግሌዎች ፊት ለፊት መሬት በተነጠፈ ቅጠል ላይ እንዲቀመጡ ይደረግና በባልዲ ይዘው የመጡት ማር ተከፍቶ በቅድሚያ የሴቷ አባት ማር በማንኪያ ለሁለቱ ተጋቢዎች ተራ በተራ እያጎረሰ ይመርቃቸዋል። በተመሳሳይ እናትም ከማሩ እያቀመሰች ትመርቃለች። በባዳዋቾ አካባቢ ምርቃት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ሲሆን በአብዛኛው ለምርቃት ተመራጭ የሚሆነው ማርና ሙሉ የሆነ ነገር (ለስላሳ፣ ውሃ) ነው። ምክንያቱም ማር ጣፋጭ በመሆኑ የትደር ሕይወታቸው እንደማር እንዲጣፍጥ ለመመኘት ሲሆን ሙሉ ነገር የሚመረጠው ደግሞ ምንም ነገር እንዳይጎድልባቸው መልካሙን ለመመኘት መሆኑን አቶ ገደቦ ገበየሁ ይናገራሉ። ከወላጆች ምርቃት ቀጥሎ የሴቷ ወገን ቤተሰቦችና ጎረቤቶች ተራ በተራ ይመርቋቸዋል። አቶ አልከሞ አሎንጆ ቤት መስከረም 20 ቀን 2011 ዓ/ም በምልከታ እንደተመለከትኩትና እንደሰማሁት በምርቃቱ ዐውድ የሚባሉ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጓሜ ያላቸውና ሁለቱ ተጋቢዎች በቀጣይ የሚመሰርቱት ትዳር የሰመረ እንዲሆን መልካም ምኞትን የሚገልጹ ናቸው። ከምርቃቶቹ መካከል "ሙሉ ሁኑ (ወም ኢኬ)፣ እንደማር ጣፍጡ (መረጵስ ጠለኤ) ብዙ ተባዙ (በረከቴ ፍካኔ)" የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ምርቃቱ እንዳበቃ እቤት ውስጥ ለነበሩ ሁሉ ትንሽ ትንሽ ማር በሲኒ እየተደረገ እንዲቀምሱ እና ሁሉም እርስ በእርስ እንዲመራረቁ ይደረጋል። ይህ የሚደረግበት ምክንያት "በሽምግልናው የመጀመሪያ ስምምነት መጽደቁን ለማረጋገጥ ነው።" ማር በጋራ ከተቃመሱ በኋላ ሁለቱ ቤተሰቦች በይፋ ዝምድናቸውን አረጋግጠዋል ማለት ነው። ስለዚህ መንገድ ላይ ቢገናኙ ሰላምታ ይለዋወጣሉ፤ዝምድናቸውን ሊያበላሽ ከሚችል ነገር እራሳቸውን ይቆጥባሉ።

#### 4.1.2.4 የሠርግ ሥነ ሥርዓት ምርጫ

የጥሎሽ ሥነ ሥርዓቱ ሲያበቃ ሠርጉ ምን ዓይነት ይሁን? የሚለውን ለጥየቃ የሄዱ ሽማግሌዎችና የሙሽሪት ቤተሰቦች ተነጋግረው ይወስናሉ። የሠርጉ ዓይነት ደጋሾቹ ባላቸው የኢኮኖሚ አቅም የሚወሰን ሲሆን እንደሚጠራው ሰው መጠን ኪፋ እና ኢልሞቻ በመባል ይታወቃል። ሠርጉ ኪፋ በሚሆንበት ጊዜ የሰው ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ ሲሆን ድግሱም ሰፋ ያለ ነው። በዚህ የሠርግ ዓይነት የሚደግስ ደጋሽ ሙሽራውን ከነአጃቢዎቹ አብልቶ አጠጥቶ አሳድሮ መመለስ ይኖርበታል። ከምግብና ከመጠጡ በተጨማሪ አጃቢዎቹ የተነጠረ ቅቤ በኩባያ መጠጣት አለባቸው። ስለዚህ ሰፊ ዝግጅትን ይጠይቃል። ይህም የሙሽሪትን ቤተሰብ የሚያስከብር ሲሆን ሚስት ተደርጋ የምትመጣዋም ሴት ሁልጊዜ ስትከበር ትኖራለች።ሠርጉ ኢልሞቻ በሚሆንበት ጊዜ የአጃቢዎችን ቁጥር የሚወስኑት የሴቷ ቤተሰቦች ሲሆኑ ድግሱም ሆነ የአጃቢው ቁጥር ከሀምሳ ሰው መብለጥ የለበትም። ድግሱ መለስ ያለ በመሆኑ ብዙ አጃቢ ይዘው እንዲመጡ አይደረግም። እንዲሁም ውለው አድረው አይወጡም። ሙሽራውና አጃቢዎቹ እንደመጡ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ እንዲበሉ ይደረግና የተዘጋጀው ስጦታ ተሰጥቷቸው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

በኪፋ የሠርግ አይነት የሚያገባ አግቢ ሙሽሪትን ለማምጣት ከአጃቢዎቹ ጋር ሲሄድ ውሎ አድሮ ለመመለስ እንደሆነ ስለሚታወቅ ዝግጅቱ ሰፋ ያለና የደጋሾችን አቅም የሚጠይቅ ነው። ሙሽሪትን ይዘው ሲመለሱም ከቤተሰብ የሚሰጣቸውን የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው እየጨፈሩ ሲሆን ይዘው ከሚመጧቸው ዕቃዎች መካከል ከሙሽሪት እናት የሚሰጡ የተለያዩ የስንደዶ ዕቃዎች (ሰፌድ፣

ወንፊት) ከአባት የሚሰጡ ከብቶች ይጠቀሳሉ። አጃቢዎቹም ይህንን ለመግለጽ ወይፈንና ጊደር አባቷ ሰጥቶናል (አዲቾ ባራ አኒም ኡዋኮ) እያሉ የተሰጣቸውን ሙሉ የቤት ዕቃ ስም እያንዳንዱን እየዘረዘሩ የሙሽሪትን ቤተሰቦች እያሞጋገሱ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

በባዳዋቾ አካባቢ ሠርግ ለመደገስ ተመራጭ የሆኑ ወራት ታህሳስ፣ ጥር ሲሆኑ አልፎ አልፎ ከነዚህ ወራት ውጪ የሚከናወኑ ሠርጎች ይኖራሉ። በመስከ ቆይታዬ ወቅት የተመለከትኳቸው ሦስት ሠርጎች ጥር 02/2012፣ ጥር 15/2012 እና ታህሳስ 5/2012 ዓ/ም የተከናወኑ ነበሩ። ታህሳስና ጥር እህል በብዛት የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ ለመደገስ አስቸጋሪ አይሆንም ብለው ስለሚያስቡና የሚጠራውም ሰው ገንዘብ አይቸግረውም ተብሎ ስለሚታመን እነዚህ ወራት ተመራጭ ናቸው። ከነዚህ ውጪ የሆኑ ወራት ላይ የሚደረጉ ሠርጎች ደጋሾችን ብቻ ሳይሆን ታዳሚውም ሠርግ ቤት ሲሄድ ይዞ የሚሄደውን ስጦታ ለማዘጋጀት ስለሚቸግረው የብሔረሰቡ አባላት ደስተኛ አይደሉም።

### 4.2 በጋብቻ ሂደት የሚከናወን ሥነ ሥርዓት

በሀድያ አካባቢ በተከናወኑ ሠርጎች ላይ በመገኘት በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ተሰብስበዋል። አጥኚው በተመለከታቸው ሦስት ሠርጎች ከዝግጅታቸው አንጻር ሰፊ ድግስ መሆን አለመሆን ከሚለያቸው በቀር አብዛኛው ሥነ ሥርዓት ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም ጥር 02/05/12 ቅዳሜ በምስራቅ ባዳዋቾ ወረዳ በዌራ ጌሬ ቀበሌ በአቶ ቢኒያም አንሼቦና በወ/ት ምህረት ለንቲሶ የሠርግ ሥነ ሥርዓት ላይ በመገኘት ከጠዋት 2:00 እስከ ማታ 4:00 የነበረው ክንውን በቅደም ተከተል ከዚህ በታች ተተንትኖ ቀርቧል።

#### 4.2.1 በሙሽራው ቤት የነበረ ሥነ ሥርዓት

በሠርጉ ዕለት ከቀኑ እስከ ስድስት ሰዓት ባለው ጊዜ ቤተሰብ ለድግሱ የሚበላውንና የሚጠጣውን በማዘጋጀትና የተዘጋጀውን በማቀራረብ ሥራ ላይ ተጠምደዋል። የሙሽራው ጓደኞች ድንኳን ውስጡን በማስዋብ ሌሎቹ ደግሞ በጭፈራ ሰፈሩን አድምቀውታል። ከቀኑ 7 ሰአት ላይ ሙሽራውና ሚዜዎቹ ሱፍ ለብሰው ወደተዘጋጀላቸው ሥፍራ እንዲወጡና እንዲቀመጡ ተደረገ። ሙሽራው ከአራት ሚዜዎቹ ጋር በመሆን ከአጃቢዎቻቸው ጋር እየጨፈሩ በተዘጋጀላቸው ቦታ ለተወሰነ ሰዓት ቁጭ አሉ። የሙሽራው አባት እና እናት ከጓደኞቻቸው ጋር በተዘጋጀላቸው ቦታ ሆነው የሚገባው ሰው በትክክል መስተናገድ አለመስተናገዱን ይመለከታሉ።

በሀድያ ባህል መሠረት ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ቤት የመስራት አቅም ካለው አባቱ በሚሰጠው መሬት ማለትም አባቱ ቤት ጎን ቤት ይሰራል። አቅም ከሌለውና መስራት የማይችል ከሆነ አባቱ ቤት ይሰራለታል። ነገር ግን አባትም ሆነ ልጅ አቅም ከሌላቸው ከእናት ከአባቱ ጋር አንድ ላይ እንድትኖር ሚስት ማግባቱ የተለመደ መሆኑን አቶ አንሼቦ ማሞ ይናገራሉ።አጥኚው በተመለከተው በአቶ አንሼቦ ቤት ሠርግ ላይ ሙሽራው (ቢኒያም አንሼቦ) ከአባቱ ቤት ጎን በተሰጠው ቦታ ቤት በመስራቱ የአባቱ ቤትና የልጁ ቤት ጎን ለጎን መሆኑን ነው።

ከስድስት ሰዓት እስከአስር ሰዓት ባለው ጊዜ ለአጃቢና ለእድምተኛው በተዘጋጀ ቦታ እንደአመጣጣቸው እየበሉ እየጠጡ ይወጡና ጭፈራ ይጀምራሉ። የሙሽራው አጎቶችና አክስቶች

ወደ ሠርጉ ቤት ሲመጡ አስር ሰውና ከዛ በላይ አስከትለው ስጦታዎችን ይዘው ወደ ግቢው ሲደርሱ ጭፈራውን ደመቅ አድርገውና ከቤተሰቡ ጋር በጋራ ጨፍረው በተዘጋጀላቸው ወቦታ ይቀመጣሉ። ይዘው ከሚመጡት ስጦታ መካከል በግ እና "ወጨት" ሲሆን ወጨቱ ውስጥ የሚኖረው ቅቤና የተለያየ ባህላዊ ምግብ ነው።

የመረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት "ሰው አስነስቶ የመግባቱ ሥነ ሥርዓት የቤተሰቡን ትልቅነት፣ ከሰው ጋር ያላቸው የመግባባት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳዩበት እንዲሁም ብዙ ዘመድ እንዳላቸው የሚያስመሰክሩበት ነው።"

አስር ሰዓት ሲሆን የሙሽራው ቤተሰቦች "ሙሽራውን በሠላም ደርሰህ በሰላም ተመለስ" ብለው ከመረቁት በኋላ ለሙሽራው፣ ለሙሽሪትና ለሚዜዎች ብቻ በተዘጋጀ ሚኒባስ መኪና ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። ሌሎች አጃቢዎች አብዛኞቹ በእግር ያጀቡት ሲሆን የተወሰኑት በሞተር ሳይክል ይከተሉት ነበር።

ሙሽሮች ለሠርግ መኪና ከመጠቀማቸው በፊት በነበረው ሥርዓት ሙሽሪት ከቤት ስትወጣ መጀመሪያ ፈረስ (ገኒቾ) ላይ እንድትቀመጥ ይደረግና ወደ ሙሽራው ቤት ጉዞ ስትጀምር በበቅሎ ላይ ተቀምጣ የወንዱ አንደኛ ሚዜ እንዳትወድቅ ከኋላዋ ሆኖ በመደገፍ ነበር "በቅሎ ስለማትወልድ ቀድማ ከተቀመጠች ልጅ ላይኖራት ይችላል  በሚል ስጋት ቀድማ ፈረስ ላይ ትቀመጥና በቀጣይ ወንድና ሴት ልጆችን እንድትወልድ በመመኘት ቀጥሎ በቅሎ ላይ ትሆናለች። በቅሎ ላይ የምትሆነው በቅሎ እንደፈረስ ስለማትፈጥንና ቀስ ብላ ስለምትሄድ ሙሽሪት እንዳትወድቅ  በማሰብ ነው።"

ሙሽራው ሙሽሪትን ለማምጣት ከቤት የወጣው አስር ሰአት ላይ ሲሆን የሙሽራው የቅርብ የሆኑ ቤተሰቦችና ጎረቤቶች ሙሽራውንና ቤተሰቡን የሚያሞግሱ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን እየዘፈኑ ሠርግ ቤቱን አድምቀውታል። በእለቱ ሲዜሙ ከነበሩ የሀድይኛ ዘፈኖች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡-

**አማርኛ**

እንደምሽት ጸሀይ አጓጊ ውበቱ
እንደትኩስ ወተት የዘረ ደማቅ ልጅ
እንደዋዲያት ቅቤ የዘረ ደማቅ ልጅ
ለጋጣ ፈረሱ ባዝራ ነው መተኪያው
ለጋጣ ላሞቹ ጥጃ ነው መተኪያው
ለምርጡ ቆጮም አለ መተኪያው
ታላቢ ከብቶቹ ቡሬ ጭራ ነጫጮች
አላቢ ጎረምሳው ጠንካራ ነው ጡንቻው
የምታልበዋም ባለ አምባራሟ ናት

**ሀድይሳ**

ማሮ ጨሚን ሜሌሾዳኖ
ሳይ ኢበዷን ሱል ኢባል ቤቶ
ኪሬ ቡሪኔ ኬማል ግች ቤቶ
ጎል ፈረዲና ጋኑዊላጎአ
ጋዲር ሳይና ጎርባ ለጎአ
ጎጆ ዋሲና ጋናሞ ለጎአ
ጎሻካም ለር ጎንዳል ሙከላ
ጎሾ ወራድ ጎቤ ደሙዋ
ጊሚሸሞት ጉማ አሞቴ

ከላይ የቀረበው የሥርግ ዘፈን ግጥም የሚያስተላልፈው መልዕክት የሙሽራውን እና የቤተሰቡን ትልቅነት ነው፡፡ ከግጥሞቹ መካከል የተወሰኑትን ስንመለከት እንደ ትኩስ ወተት የዘረ ደማቅ ልጅ (ሳይ ኢበደኔ ሱል ኢባል ቤቶ) በሚለው በባዳዋቾ ሀድዮች ዘንድ የሀብት መጠን የሚለካው ባሉት በርካታ ከብቶች በመሆኑ ያለውን ከብት ዓይነትና ብዛት እየዘረዘሩ የሙሽራው አባት ሀብታም መሆኑን የሚገልጹበት የሥርግ ዘፈን ነው፡፡ በዚሁ የሥርግ ግጥም ላይ በሌላ አንድ ስንኝ አላቢ ጎረምሳው ጠንካራ ነው ጡንቻው (ጎሾ ወራድ ጎቤ ደሙዋ) የሚለውን ስንመለከት በባዳዋቾ አካባቢ ወተት የማለብ ሥራ የሴቶች እንደሆነ ነው የሚታወቀው ነገር ግን የሙሽራው አባት በርካታ የሚታለቡ ከብቶች ባለቤት ከመሆኑ የተነሳ የማለቡ ሥራ ከሴቶቹ አቅም በላይ ሆኖ ጡንቻ ያለው ወንድ እንዳስፈለገ በግጥሙ አማካይነት ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡

አጥኚው በመስክ በነበረው ቆይታ በተመለከታቸው ሠርጎች ሙሽራው ከቤት ሲወጣ የሚዘፈኑ ዘፈኖች በአብዛኛው ሙሽራውንና የሙሽራውን ቤተሰቦች የሚያሞጋግሱ ማለትም የብዙ ከብት ባለቤት መሆናቸውንና ሙሽራው የሀብታምና የትልቅ ሰው ልጅ መሆኑን ለታዳሚው መንገሪያ ናቸው፡፡

### 4.2.2 በሙሽሪት ቤት የነበረው ሥነ ሥርዓት

ሙሽሪት የነበረችበት ቤት እንደደረሱ ለተወሰነ ሰአት በር ላይ ቆመው ሙሽሪትንና ሙሽራውን የሚያሞግሱ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍኑ ነበር፡፡ ሙሽሪት ቤት በወንዱ አጃቢዎች የሚዜሙ ዜማዎች የወንዱን ትልቅነትና ሀብታም መሆን የሚገልጹ ሲሆን የሴቷ ወገኖች በምላሹ ወንዱ የሚያገባት ልጅ ከሱ የተሻለች በመሆኗ እሷን በተገቢ ሁኔታ ማስተዳደር እንደማይችል የሚያበላት ነገር እንኳ እንደሌለው ወይም ያለው ነገር የሱ እንዳልሆነ እየተናገሩ የሠርጉን ቤት ያደምቁታል፡፡ የመረጃ ሰጪዎቼ እንደሚናገሩት በሠርግ ወቅት አንዱ ከአንዱ የተሻለ እንደሆነ ለማሳየት በሠርግ ግጥሞች አማካይነት የሚባሉ ነገሮች የተጋነኑ ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ቢኖርም አላማው በእለቱ ያለውን የሠርግ ድባብ ከማሞቅ ያለፈ ነገር ስለማይኖረው በየትኛውም ወገን ያለ ሰው ተሰደብኩ ወይም የማይሆን ነገር ተባልኩ በሚል ቅያሜ ውስጥ አይገባም፡፡ ከዚህ በታች የወንዱ አጃቢዎች ለሴቷ የሴቷ አጃቢዎች ደግሞ ለወንዱ ያዜሙት ዘፈን ቀርቧል፡፡

**አማርኛ**

በቅቤ የታሸ የገበስ ቆሎ
ጩኮ ወጪት
በቅቤና ምስር ዱቄት የሚሰራ ምግብ
የፋሲካ እንጀራ
በጣም በማለዳ
ከብት ማለብ ከቻልሽ
ባልንጀራ በሚጠራሽ ማለዳ
ማብሰል ከቻልሽ
በሌሊት ድረሺ

በባዳዋቾ ሀድዮች ዘንድ በሠርግ ሥነ ሥርዓት በዋናነት ከሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች ውስጥ ከላይ በዘፈኑ ውስጥ የተዘረዘሩ ምግቦች ይጠቀሳሉ። እነሱም ጩኮ፣ ሃነቀላ፣ ሃንሳቤሎ፣ ቡሎ ወዘተ. በመሆኑም ሙሽሪትን እነዚህን ባህላዊ ምግቦች መስራት የምትችል ባለሙያ እንደምትሆን ይገመታል። ነገር ግን የወንዱ እህቶችና ጓደኞቻቸው ተሰባስበው "ከላይ የተዘረዘሩ ምግቦችን መሥራት የማትችይ ሙያ የሌለሽ ሴት በመሆንሽ ለወንድማችን አትገቢውም" እያሉ ሲያዜሙ የሴቷ ወገኖች ደግሞ አጸፋውን ሲመልሱ "ማግባቱንስ ያግባ ግን ምን ያበላታል፤የትኛውንስ ከብት ያሳልባታል፤ አንዲት ላም ብትኖረው እሷም የጋራ ናት" በማለት ደሃ መሆኑንና ሙሽሪት ከሱ የተሻለች መሆኗን እንደሚከተለው ይመልሳሉ፡-

**አማርኛ**

መሄዱንስ ትሂድ
ምን ያርድላታል
ምን ያስልባታል
አንዷም ከሲታ ላም
ከዘመድ የእኩል ናት
ኮርማ በሚቆምበት
ሙቀጫ ቆሟል
እንደጠገራ እንጨት
ሌጣ ነው ልጁ

**ሀድይኛ**

መራ መተሞ
መ ቡች ለጎ
ማ ጎሺሶ
ሜቴም አሚች
ሞሊ ኮታአ

ሞር ኡሎ ቤዮኔ
ሞዬ ኡላኮ
ሜሳኒ ሃቂኔ
ሙድል ኤቤቶ

ሙሽራውና አጃቢዎቹ ወደሙሽሪት ቤት ሲደርሱ ሙሽራዋ ያለችበት ቤት ዝግ ሆኖ ስለሚቆይ እየጨፈሩ ይቆዩና ከፊት የነበሩ የወንዱ ሙሽራ አጃቢዎች በሩን በሀይል ከፍተው ወደ ውስጥ ዘልቀው ሳይቀመጡ ሙሽሪትንና ሚዜዎቿን ይዘው ይወጣሉ። በባዳዋቾ ሀድዮች ባህል መሰረት አንዲት ሴት በቤተሰብ ስምምነት ታጭታ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተሟልቶ የሙሽሪት ቤተሰቦች የመደገስ አቅም ከሌላቸው የሠርጓ ቀን ሲደርስ ለሙሽራው ቤት አቅራቢያ ካሉ ዘመዶች የአንዱ ቤት ይመረጥና ከዛ ቤት ተሞሽራ እንድትወጣ ይደረጋል።

አጥኚው በተገኘበት በአቶ ቢኒያም አንሼቦ ሠርግ የሙሽሪት ቤተሰቦች መኖሪያ ወንዱ ሙሽራ ከሚገኝበት እሩቅ በመሆኑና በወቅቱ ድግስ  የመደገስ አቅም እንዳልነበራቸው በሽምግልናው የመጨረሻ ቀን ተነጋግረው በመወሰናቸው በወንዱ ሙሽራ ቤት አቅራቢያ የሚገኝ የዘመድ ቤት ተመርጦ እንድትሞሽር እንደተደረገ ለማየት ችሏል።

አጃቢዎች ከሙሽሪት ቤት ሊወጡ ሲዘጋጁ  በዘፈን ግጥሞቻቸው አማካይነት “ስጠንና ሸኘን” (ኡዊታ ጌጌሴ) እያሉ እንደሚሰጣቸው የሚያስቡትን (ከዚህ በፊት ሌላ ሰው ሲሰጥ ያዩትን)  የቤት ዕቃ ስም እየጠቀሱና ስጦታ ሊሰጡ የሚችሉ ቤተሰቦቿን እያሞጋገሱ የተዘጋጀላቸውን ስጦታ መቀበል ይጀምራሉ “አንዲት ሴት በሠርግ ከቤተሰቦቿ ጋ ስትወጣ ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችንና ከብቶችን ይዛ መውጣቷ የተለመደ ነው።”

ሙሽሪት በቤተሰብ ስምምነት በሠርግ ከቤተሰቦቿ ቤትም ሆነ አስቀድማ ወደ ምትሞሽርበት ቤት ስትመጣ ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚያገለግሉ የተለያዩ የስንደዶ ዕቃዎች (ሰፌድ፣ ወንፊትና መሶብ) እንዲሁም ለማረስ የደረሰ ከብት ይዛ መሄድ ይኖርባታል። አጃቢዎቹም ሙሽሪትን ይዘው ወደ ሙሽራው ቤት ሲሄዱ መንገድ ላይ የተሰጣቸውን ወይፈንና ጊደር እንዲሁም የቤት ዕቃዎች ስም በዘፈን ግጥሙ እየዘረዘሩ ይዘን መጥተናል (አመንዳ ዋላሞ)፣ ወይፈንና ጊደር አባቷ ሰጥቶናል (አዲቾ ባራ አኒም ኡዋኮ) በማለት  አባቷንና እናቷን  እያሞጋገሱ ወደ ሙሽራው ቤት ይሄዳሉ።

**አማርኛ**

ይዘን መጥተናል
ድንግል ልጃገረድ
የአባት ስጦታ ከብት
ጊደርና ወይፈን
ቁናና ወንፊት
የራስጌ የእንጨት ትራስ
ለስላሳ ቁርበት

ዘርፋም ቡልኮ

***ሀድይኛ***

አመንዳ ዋሉሞ
ለንድች ባጃሞ
አኒ ጌጋዮ ሰሮ
አዲቾ ባራ
ሳንፎ ኢላንቾ
ሱናም በርኩማ
ሱሮ ሂርፋና
ሾጋም ወያኮ

### 4.2.3 በሠርጉ ቀን የሙሽሮችና የእድምተኞች አለባበስ

በባዳዋቾ አካባቢ ቀድሞ በነበረው የአለባበስ ሥነ ሥርዓት ሙሽራው ከአቡጀዲ የተሰፋ ተነፋነፍ ሱሪ ላይ ነጭ ኮት በመደረብ ይለብስና ፀጉሩ እስኪያብለጨልጭ ድረስ ቅቤ ይቀባ ነበር፡፡ ሴቷ ደግሞ የሀበሻ ቀሚስ ለብሳ ከላይ ሹራብ ትደርብና ጸጉሯን በሻሽ ትሸፍናለች "ፊቷ በሻሽ የሚሸፍነው በባህሉ መሰረት የባሏ ቤተሰቦች ስጦታ ሳይሰጧት በቀላሉ ፊቷን ማየት እንዳይችሉ ለማድረግ ነው፡፡ " አሁን ባለው ሁኔታ ግን ወንዱ ሱፍ መግዛት ባይችል እንኳን ተከራይቶ ሴቷም ቬሎ ተከራይታ በለባበሳቸው የከተማውን የመምሰል ሁኔታ ይታያል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ አባላት ደስተኛ አለመሆናቸውንና ለአላስፈላጊ ወጪ መዳረጋቸውን ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ሙሽራዋ ምንም እንኳን ቬሎ ብትለብስ ፊቷን በማይታይ መልኩ መሸፈን ይኖርባታል፡፡ በተለይ ወደ ባሏ ቤተሰቦች መኖሪያ አካባቢ ስትደርስ ከንብብቡን የበለጠ ዝቅ ታደርገዋለች፡፡ ምክንያቱም የባሏ ቤተሰቦች ስጦታ ሳይሰጧት ፊቷን በቀላሉ ሊያዩ አይገባም፡፡

ለሠርግ የተጠሩ እድምተኞችና ቤተሰቦች የሚለብሱት ነጣ ያለ ልብስ ሆኖ ሠርገኛ የሚያስመስል መሆን ይኖርበታል፡፡ አዲስ ማሰፋት የማይቻል ከሆነ በፊት የነበረው ታጥቦና ተስተካክሎ ይለበሳል "በፊት ቁምጣ ሱሪና ከላይ ንጹህ የሆነ ልብስ ይለበስ ነበር አሁን አሁን ሙሉ ልብስ ለሠርጉ የተለየ ድምቀት ሊሰጥ የሚችል ልብስ ይለበሳል፡፡"

### 4.2.4 ማታ ወደ ሙሽራው ቤት ሲገባ የሚከወን ሥነ ሥርዓት

ሙሽሮቹና አጃቢዎቹ ወደ ሙሽራው ቤት ሲመለሱ መንገድ ላይ ከሙሽሪት ቤተሰቦች የተሰጣቸውን ስጦታ ከፍ አድርገው እያንዳንዱን እየዘረዘሩ "ይዘን መጥተናል" (አመንዳ ዋሉሞ) እያሉ በማዜም ነው፡፡

**አማርኛ**

ይዘን መጥተናል
ድንግል ልጃገረድ
የአባት ስጦታ ከብት
ጊደርና ወይፈን
ቁናና ወንፊት
የራስጌ የእንጨት ትራስ
ለስላሳ ቁርበት
ዘርፋም ቡልኮ

**ሀድይሳ**

አመንዳ ዋሉሞ
ለንድች ባጃሞ
አኒ ጌጋዮ ለሮ
አዲቾ ባራ
ሳንፎ ኢላንቾ
ሱናም በርኩማ
ሱሮ ሂርፋና
ሾጋም ወያኮ

ወንዱ ሙሽራ ቤት እንደደረሱም ለተወሰነ ሰዓት በጋራ ጨፍረው ሲያበቁ በተዘጋጀው ምግብና መጠጥ በቅድሚያ ሙሽሮቹና ሚዜዎቹ ቀጥሎ የሙሽራው ቤተሰቦችና ሙሽሮቹን ለመቀበል የመጡ ጎረቤቶች ይስተናገዳሉ። ከመስተንግዶ በኋላ የወንዱ ሙሽራ እህቶች፣ አክስቶችና የቅርብ የሆኑ ቤተሰቦች ያመጡትን ስጦታ በየተራ ያስረክቧቸዋል። ይዘው የሚመጡት ስጦታ በአብዛኛው ባህላዊ ምግብ ሲሆን ይዞ ያመጣው ሰው ማንነትና የዝምድናው ሁኔታ እየተነገረ ቅድሚያ ለሙሽሮቹና ለአጃቢዎቹ መሰጠት አለበት። በመቀጠልም ሠርጉ ቤት ለታደሙ እድምተኞች ትንሽ ትንሽ እንዲቀምሱ ይደረግና የቀረው ከነዕቃው ለሙሽሮቹ ይሰጣል። "ምክንያቱም ሙሽራው ባለብዙ ዘመድ እንደሆነ ሙሽሪት እንድታውቅና በጫጉላ ቤት ቆይታዋ ወቅት ሊጠይቋት የሚመጡ እንግዶችን እንድታስተናግድ በማሰብ መሆኑን ወ/ሮ እቴነሽ ሊሬ ነግረውኛል።"

ስጦታ የመስጠቱ ሥነ ሥርዓት እንዳበቃ ሙሽሪትና ሙሽራው ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን በጭፈራና በብዙ እልልታ ወደተዘጋጀላቸው ቤት ያመራሉ። ሙሽሪት የሙሽርነት ጊዜዋን የምታሳልፈው እቤት ውስጥ ሆኖ በመጋረጃ በተሸፈነ ቦታ ሲሆን ይህም "ዱማ" በመባል ይታወቃል።

ሙሽሮቹ ወደ ዋናው በር ሲጠጉ የሙሽራው እህቶች "አናስገባም" በማለት በሩን ይዘው ይቆማሉ። ለሙሽሮቹ በር የሚለቁት እና የሚያስገቧቸው የወንዱ ሚዜዎች የብር ስጦታ ከሰጧቸው በኋላ ነው። እስከዛው ግን እውጭ ያሉትም እቤት ውስጥ ያሉትም በህብረት ጭፈራ ድባቡን

ያደምቁታል። እህቶቹ የተሰጣቸውን ስጦታ እንደተቀበሉ የያዙትን በር ይለቁና ሙሽሮቹን ወደ ውስጥ ያስገቧቸዋል። በዚህ ሁኔታ ሙሽሮቹ ከነሚዜዎቻቸው ወደቤት ሲገቡ ሌሎች አጃቢዎች ወደኋላ በመመለስ ውጭ በተዘጋጀው ድንኳን ውስጥ ገብተው መጨፈራቸውን ይቀጥላሉ።

### 4.2.5 በሠርግ ወቅት የሚዘጋጁ ምግብና መጠጦች

በሀድያ ብሔረሰብ ዘንድ በሠርግ ዕለት የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች አሉ። ከነዚህ መካከል በቡላና አይብ የሚሰራ (አተካና)፣ ከገብስ ዱቄት የሚሠራ (ሶቡሎ)፣ በገብስ ዱቄት ያለውሃ በቅቤ ብቻ የሚሰራ ጨኮ፣ የገብስ ቆሎ በቅቤ ታሽቶ የሚዘጋጅ ሀነቀላ፣ አይብ በቂጣና በቆጮ በዋናነት ይጠቀሳሉ። ሁሉም ባህላዊ ምግቦች ብዙ ቅቤ ሊኖራቸው ይገባል።

ከላይ ካየናቸው በሠርግ ወቅት ከሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች መካከል ሀነቀላ አንዱ ሲሆን ሦስት ዓይነት አዘገጃጀት ወይም ደረጃ አለው። የመጀመሪያው "ሂነቀላ"፣ ሁለተኛው "ሀነቀላ" ነው። ሁለቱም ከገብስ ቆሎ የሚዘጋጁ ሲሆኑ በጣም በቅቤ የታሹና ለተከበረ እንግዳ የሚቀርቡ የሀድያ ብሔረሰብ የባህል ምግቦች ናቸው። የሚጠጣ በአብዛኛው ከገብስ ከቦቆሎና ከማሽላ የሚሰራ (ቦርዴ)፣ ሻሜታና አረቄ በብዛት ይዘጋጃል።

### 4.2.6 ለሙሽሪት ስም የማውጣት ሥነ ሥርዓት

በሠርግ ዕለት ምሽት የወንዱ ሙሽራ ቤት ከሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች መካከል አንዱ ለሙሽሪት ስም የማውጣት ሥነ ሥርዓት ነው። ይህም በቤተዘመድ የሚሰጠው የስጦታ ጊዜ እንዳበቃ የሚከናወን ሲሆን የራሱ የሆነ ቅደም ተከተል አለው። የስም አወጣጡን ስንመለከት በብሔረሰቡ ባህልና ወግ መሰረት በቤተሰቡ ውስጥ ባሉ ወንዶች ልጆች ቅደም ተከተል ሲሆን የመጀመሪያ ልጅ ሚስት ከሆነች ቀዳማዊት (ሉደጌ)፣ የሁለተኛ ልጃቸው ሚስት ከሆነች ተከተይ (አወኔ)፣ የሦስተኛው ልጅ ሚስት ከሆነች ከሁሉ የምትስማሚ (ታጳኔ)፣ የአራተኛ ልጅ ሚስት ከሆነች ተከበሻል (ክበሜ)፣ አምስተኛ ከሆነች አስከባሪ (ኬሚሴ) የሚል ነው።

በ02/05/12 አጥኚው በተመለከተው በአቶ ቢኒያም አንሼቦና ወ/ት ምህረት ለንቲሶ ሠርግ አቶ ቢኒያም ለቤቱ የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ የሙሽራው እናት ሙሽሪትን ቀዳማዊት (ሉደጌ) ብለው ስም አውጥተውላታል።

ሙሽሪት ሙሽራው ቤት እስካለች ድረስ የሙሽራው ቤተሰብ የሆኑ ሁሉ የሚጠሯት በአዲሱ ስሟ እንጂ የድሮውን ስም መጠቀም አይችሉም። ባሏ ግን በመደበኛ ስሟ መጥራት ይችላል። ሙሽሪት የትዳር አጋርዋን (ባሏን) የምትጠራው በአክብሮት አንቱ (ኪኔ) ብላ ሲሆን ልጅ ከወለደች በኋላ ግን ለልጁ አባት መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ በመጀመሪያ ልጁ ስም መጥራት ይፈቀድላታል "የመጀመሪያ ልጁ ስም ጫኪሶ ቢሆን ባሏን የጫኪሶ አባት (ጫኪስ አና) ብላ መጥራት ትችላለች።
"

## 4.3 በድህረ ጋብቻ የሚከወን ሥነ ሥርዓት

ሙሽራውና ሙሽሪት ከጋብቻ በኋላ የሙሽርነት ጊዜያቸውን በተለያየ ሁኔታ ያሳልፋሉ። ይህ የቆይታ ጊዜ በተለይ ለሴቷ ሙሽራ ከባሏ ቤተሰቦች ጋር የምትተዋወቅበትና ያላትን ሙያ የምታሳይበት በመሆኑ እያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት በትኩረት ይከናወናል።

### 4.3.1 የጫጉላ ቤት ሥነ ሥርዓት (ዱማ)

ሙሽራውና ሙሽሪት ከሠርጋቸው በኋላ የሚቆዩበት ቦታ "ዱማ" ይባላል። የጫጉላ ቤቱ የሚሠራው ከሠርጉ አንድ ቀን በፊት በሙሽራው ሚዜዎችና ጓደኞች አማካይነት ነው። ሙሽሪት በሙሽርነት ጊዜዋ በፊት ለፊት በር ስትወጣና ስትገባ ሰው እንዲያያት ስለማይፈለግ በጓሮ በር የምትወጣበትና የምትገባበት "ፋለኤ" (የጓሮ በር) ይዘጋጅላታል "ሰው እንዲያያት የማይፈለገው በሀድያ ባህል መሰረት ሙሽሪትን ማየትና መተዋወቅ የሚፈልግ የባሏ ጓደኛም ሆነ ቤተሰብ ስጦታ ይዞ በመምጣት በመሆኑ ስጦታ ላላመጣ ሰው ፊት ለፊት አትታይም።"

በአብዛኛው ለሙሽሮቹ የሚዘጋጀው ቦታ በቤቱ ጓዳ ሲሆን ዙሪያው በመጋረጃ ተሸፍኖ ሙሽሪትን ማንም ሰው ሊያያት በማይችል ሁኔታ የምትቀመጥበት አይነት መሆን ይኖርበታል። የሠርጉ ዕለት ማታ ሙሽሪት ወደተዘጋጀላት የተከለለ ቦታ ከመግባቷ በፊት በር ላይ እግሯን ዘርግታ እንድትቀመጥ ይደረግና አንድ ወንድና አንዲት ሴት ህጻን ልጅ ላይዋ ላይ በማስቀመጥ ሙሽሪት በትዳር ቆይታዋ ወንድና ሴት ልጆችን አፈራርቃ እንድትወልድ በሽማግሌዎች አማካይነት "ወንድና ሴቱን ውለጂ (ጎንቺ ለንዲቺ ቀረሞና)" በማለት ትመረቅና ወደተዘጋጀላት ቦታ ትገባለች።

ከሠርጓ ቀን በኋላ የባሏ ዘመድ የሆኑ ጠያቂዎች ወደ ቤቷ ሲመጡ የተለያዩ ስጦታዎችን በመያዝ ሲሆን ስጦታ ይዞ ላልመጣ ሰው ሙሽሪት ፊቷን አታሳይም። "ምክንያቱም በቀጣይ የትዳር ቆይታዋ የምትከበረው በባህሉ መሰረት መደረግ ያለበት ተደርጎ መሆን አለበት። ድንገት ከተከለለው ቦታ ወጥታ ባለችበት የባሏ ቤተሰብ የሆኑ ሰዎች ሊተዋወቋት ከመጡ እሮጣ ወደ ውስጥ በመግባት ትደበቃች። እሷን ለማየት የሚፈልግ ቤተሰብ የተለያዩ ስጦታዎችን (እርፎ) ይዞ በመምጣት መሆን አለበት።" ስለዚህ አስቀድመው ማንነታቸውንና ስጦታቸውን በመላክ እንድትወጣ አድርገው ይተዋወቋታል። በመሆኑም ስጦታ ከሰጧት ሰዎች ጋር ብቻ ፊት ለፊት ተገናኝታ ታወራለች።

የሙሽሪት የጫጉላ ቆይታ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በመሆኑ ከዛ በፊት ከቤት እንድትወጣ አይፈቀድላትም። የጫጉላ ጊዜዋን የምታሳልፈው ወደፊት ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚሆኑ በስንደዶ የሚሰሩ ዕቃዎችን ማለትም ሰፌድ፣ ወንፊትና መሶብ የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ሥራ ተጠምዳ ነው። ይህ ወቅት ሙሽሪት ጊዜዋን በሥራ የምታሳልፍበት ብቻ ሳይሆን ባለሙያ መሆኗን ለባሏ ቤተሰቦች የምታሳይበት እንደሆነም ይታመናል። እንዲሁም የባሏን የቅርብ ቤተሰብ የሆኑትን ማለትም አጎት አክስት ማክበር ስላለባት እነማን እንደሆኑ በሙሽራው እህቶች አማካይነት ይነገራታል "በባዳዋኞ ሀድዮች ባህል ሙሽሪት የባሏን እናት፣ አባት፣ ታላቅ እህትና ወንድም እናንተ (ኪኔ) ብላ በአክብሮት መጥራት ይኖርባታል። ከዚህ ውጪ ስትጠራ ከተሰማች የባሏን ቤተሰቦች እንደማታከብር ስለምትቆጠር በቤተሰቡ ዘንድ ተወዳጅ አትሆንም።"

ሙሽሪት ከጫጉላ ቤት መውጫዋ ሲደርስ ወደውጪ ከመውጣቷ በፊት የቤት ውስጥ ሥራዎችን መሥራት ትጀምራለች። ሥራ ስትጀምር ቀለል ካለው ቡና ማፍላት፣ ቤት ማጽዳት ትጀምርና ከብት ወደ ማለብ፣ እንሰት ወደ መፋቅና ሌሎች ከባድ ሥራዎች ቀስ በቀስ ትሸጋገራለች። ወደ ውጪ ስትወጣ የሙሽርነት ጊዜ (እዳያኖ) ላይ መሆኗን በሚያሳውቅ መልኩ የተለያዩ ጌጣጌጦችን በጆሮዋ፣ በእጇና በአንገቷ ላይ ታደርጋለች። በመሆኑም የሚያያት ሁሉ አለባበሷንና አጋጊያጧን ብቻ በማየት ማንም ሰው ሳይነግረው ሙሽራ መሆኗን በቀላሉ ይለያል።

### 4.3.2 የመልስ ሥነ ሥርዓት (ኢል ኤጃ)

በድህረ ጋብቻ ከሚከናወን ሥነ ሥርዓት ሌላው ተጠቃሽ መልስ ነው። ከሠርግ በኋላ ለሙሽራውና ለሙሽሪት ቤተሰቦች የሚመች ቀን ተመርጦ የመልስ ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። በመልስ ቀን ወደ ሙሽሪት ቤት ሲኬድ ለእናት የሚለበስ ልብስና በግ እንዲሁም ለአክስትና አጎቶቿ የሚሆን የተለያየ ስጦታ ተይዞ መሆን አለበት “መልስ በሚሄዱበት ጊዜ ሙሽራውንና ሙሽሪትን ከነሚዜዎቻቸው ሁለትና ሦስት ቀን አሳድረው አብልተው አጠጥተው ይሸኟቸዋል።” ሦስት ቀን አሳድሮ መመለስ አሁንም የሚተገበር ሲሆን አቶ ኦልከሞ ኦሎንጆ ሴት ልጃቸውን ወ/ሮ ኤልሳ ኦልከሞንና አቶ ገብሬ ታደሰን መስከረም 14 ቀን 2012 ዓም እሁድ ዕለት ጠርተው ማክሰኞ ምሽት መሸኘታቸውን ታይቷል። በሦስቱም ቀን የሚከናወነው ሥነ ሥርዓት የተለያየ ሲሆን አጠቃላይ ሂደቱ ከዚህ በታች ተተንትኗል።

የመልሱ ቀን ሙሽሮቹና አጃቢዎቹ ወደሙሽሪት ቤተሰብ ቤት የደረሱት አመሻሽ ላይ ነበር። እቤት እንደገቡም ለተወሰነ ደቂቃ በዝምታ ከተቀመጡ በኋላ ከሙሽሪት ወገን የሆነ አንድ ሰው (የአባት የቅርብ ጓደኛ) ተነስቶ “እንኳን ደህና መጣችሁ” በማለት ሙሽራውና ሙሽሪት የሴቷን ቤተሰቦች የሚተዋወቁበት ሰዓት መሆኑን ሲናገር ሙሽሮቹ በዝምድና ቅደም ተከተል የተቀመጡ የሴቷን ቤተሰቦች በሙሽሪት መሪነት ለአባት፣ እናት፣ አክስቶችና አጎቶች ተራ በተራ ጉልበታቸውን እየሳመች የያዘችውን ስጦታ ትሰጣለች ሙሽራውም እሷን እየተከተለ የምታደርገውን ያደርጋል። የሙሽሪት ቤተሰብ የሆኑ ሁሉ በተዘጋጀላቸው ቦታ ተቀምጠው የትውውቅ ሥነ ሥርዓቱ ስለሚፈጸም እንግዶቹን የሚያስተዋውቀው የአባቷ ጓደኛ እንደሆነ አቶ ልቦና ጳውሎስ ይናገራሉ።

መልስ በተጠሩ በሁለተኛው ቀን አባት በሙሽሮቹ ስም ለማረድ ያዘጋጀውን ኮርማ (አነስ ያለ በሬ) ከመታረዱ በፊት የሴቷ ዘመዶችና የወንዱ ሙሽራ ቤተሰብ የሆኑ ሽማግሌዎች ተጠርተው በተሰበሰቡበት “ለልጆቻችን ያዘጋጀነው ኮርማ ይህ ነው ከመታረዱ በፊት ሙሽሮቹንና የሙሽሪትን ወላጆች መርቁ በናንተና በዚህ ቤተሰብ መሀል ሰላም የምትፈጥሩ ተወካይ ሽማግሌዎች እናንተ ናችሁና ኮርማውን አይታችሁ ምርቃታችሁን ስጡ” የሚል መልዕክት ከሙሽሪት ወገን በኩል በሆነው ሰው (ሲገቡ እንኳን ደህና መጣችሁ ያለው) አማካይነት ይነገራል። ከመጡት ሽማግሌዎች አንዱ ተወክሎ የሙሽሪትን ቤተሰብ መመረቅ ጀመረ። ከፍ በሉ (ሎጴ) ፣ ተባረኩ (ማሰአሜ)፣ የናንተ የሆነው ከብቱም የተወለዱ ልጆችም (ሳይም ቀቺም ኪኔ ኢለግ ኢሆና)፣ ልጆችም ይደጉ (ኦሲም ሊኦና) በማለት ቤተሰቡን ከመረቀ በኋላ የተዘጋጀው ኮርማ ወደ መታረጃ ቦታው ይወሰዳል። የሚታረደው ኮርማ ለመልሱ ከተዘጋጀው ሌላ በሙሽሪት ቤተሰቦች የሚዘጋጅ ሲሆን

“ሙሽሪትንና ቤተሰቦቿን በባሏ ዘመዶች ዘንድ የሚያስከብር እንደሆነ ስለሚታመን በባዳዋቾ አካባቢ ልጁን መልስ የሚጠራ ወላጅ ሁሉ የማድረግ ግዴታ አለበት።

የሙሽራው ቤተሰቦች የሙሽሪትን ወላጆች ከመረቁ በኋላ ቀጣዩ የምርቃት ሥነ ሥርዓት የሚሆነው መልስ ሲገቡ በባልዲ ያመጡት ማር በዕለቱ ለታደሙ ሁሉ በትንንሽ ዕቃ ከማንኪያ ጋር ቀርቦ ሙሽሪትና ሙሽራው መሬት ላይ ተነጥፎላቸው እንዲቀመጡ ይደረግና መጀመሪያ የሙሽሪት እናትና አባት ሙሽሮቹን ከማሩ ሁለት ሁለት ጊዜ እያጎረሱ “እንደማር ኑሮአችሁ ይጣፍጥ (መረጵስ ጠሌኤ)፣ ብዙ ተባዙ (በረከተኤ ፍካኔ) ተባረኩ (ማስአሜ)” እያሉ ይመርቃሉ። ምርቃቱ በአብዛኛው ሁለቱ ተጋቢዎች በትዳር ዘመናቸው መልካም ነገር እንዲገጥማቸው መልካም ምኞትን መግለጫ ነው።

በሀድያ ባህል ለመልስ ሥነ ሥርዓት ለሠርግ ሥነ ሥርዓት እንደሚዘጋጀው የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች ይዘጋጃሉ። ነገር ግን ከሠርጉ በተለየ በሦስተኛ ቀን ሙሽሮቹ ወደቤታቸው የሚመለሱ ዕለት በገብስ ዱቄት በቅቤ ተፈርፍሮ የሚዘጋጅ (ቡሎ) በትልቅ ገበቴ (ሰፊ ዕቃ) ላይ ይደረግና ሙሽራውና ሙሽሪት በጋራ እንዲቀምሱት ይደረጋል። ይህንን ገበታ በጋራ እንዲቀምሱ የሚደረግበት ምክንያት “ሁለቱ ተጋቢዎች አንድ መሆናቸውንና ከቤተሰቡ ጋር ዝምድናቸው መጠናከሩን ለማሳየት በመሆኑ ከነሱ የተረፈውን ሙሽሪት ወደባሏ ቤት ይዛ በመሄድ በቀኑ ላልተገኙ ቤተሰቦች ማቅመስ አለባት። ”

መልስ የሄዱ የሙሽራው አጃቢዎች የሙሽሪት ቤተሰቦች ካዘጋጁት ምግብና መጠጥ በተጨማሪ የተነጠረ ቅቤ አጠጥተው ፀጉራቸውንም ቀብተው መሸኘት አለባቸው። ምክንያቱም “መልስ የመጡ ሰዎች የሙሽሪትን ቤተሰብ እንዲያከብሩና የትልቅ ሰው ልጅ መሆኗን እንዲመሰክሩ ታስቦ መሆኑን አቶ መንገሻ ገበየሁ ይናገራሉ።”

### 4.3.3 የቅልቅል ሥነ ሥርዓት

የቅልቅል ሥነ ሥርዓት የሁለቱን ቤተሰብ አንድነት ማረጋገጫ ሲሆን የሚፈጸመው በወንዱ ሙሽራ ቤተሰቦች ቤት ነው። የመልስ ሥነ ሥርዓቱ በተከናወነ በሦስተኛ ወይም በአራተኛ ሳምንት ለሁለቱ ቤተሰቦች አመቺ የሆነ ቀን ተመርጦ ቤተዘመድ በተገኘበት ሙሽራዋን ከቤተሰቡ ጋር የመቀላቀል ሥነ ሥርዓት ይከናወናል። በዕለቱ ሙሽራዋ ከነበረችበት ጓዳ ወደፊት ለፊት ከመውጣቷ በፊት ሚዜዎቿ እየዞሩ ከተሰበሰበው ቤተሰብ ስጦታ ይሰበስባሉ። ስጦታው ትርጉሙ “ከዚህ በኋላ ከኔ እንዳትሸሽ” የሚል ነው። የባሏ የቅርብ የሆኑ ሁሉ በዕለቱ በሚደረገው የቅልቅል ሥነ ሥርዓት ስጦታ እየሰጡ ካልተዋወቋት ሁልጊዜ ያንን ሰው ባየች ቁጥር ትደበቃለች።

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የሀድያ ብሔረሰብ አባላት በባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጽሟቸውን ክዋኔዎች ከዐውዳቸው በመሰብሰብ ያላቸውን ትርጉም መግለጽና መተንተን ላይ አተኩሮ የተሰራ ነው። በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በተመረጡ ሁለት ወረዳዎች ከነበሩ የጋብቻ ሥነ

ሥርዓቶች በሦስት ሠርግ፣ በአንድ መልስ እንዲሁም በአንድ የጋብቻ ጥየቃ ተፈጥሮአዊ ዐውድ ላይ በመገኘት መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው ተተንትነዋል።

በተገኙ መረጃዎች መሰረት በሀድያ ብሔረሰብ የሚከናወኑ የጋብቻ ዓይነቶች አራት ሲሆኑ ከነዚህ መካከል በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚታወቀውና ተቀባይነት ያለው ሉዲሻ (በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም) የጋብቻ ዓይነት ነው። በዚህ የጋብቻ ዓይነት መጀመሪያ የሚቀድመው የተጋቢዎች መፈላለግ ወይም የወላጆቻቸው በጋብቻ ለመዛመድ መፈላለግ ነው። በመሆኑም አንድ ወንድ የሚያገባትን ሚስት በሁለት መንገድ ሊመርጥ ይችላል። የመጀመሪያው ወንዱ ልጅ እራሱ የሚያገባትን ሴት አስቀድሞ መርጦ የወደዳትን ልጅ ማንነት፣ የማን ልጅ እንደሆነችና አድራሻዋን ለቤተሰቦቹ ይናገርና ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ዘንድ ሽማግሌ ያስልካል። ሁለተኛው የወንዱ ልጅ ወላጆች በአካባቢው ካሉ ልጃገረዶች ለልጃቸው ትሆናለች ብለው የሚያስቧትን የሚመርጡበትና ለልጃቸው የሚያሳውቁበት ነው። በጥናቱ እንደታየው በቤተሰቦቹ የተመረጠችለትን ሴት ካልወደዳት ያለማግባት መብቱ የተጠበቀ ነው። የተመረጠችውም ሴት ልጁን አይታ ካልፈለገችው እንድታገባው አትገደድም። የመመራረጡ ሂደት ሲያበቃ በአካባቢው ተሰሚነት ያላቸውና የማሳመን ችሎታ ያላቸው ሽማግሌዎች ተመርጠው ለጋብቻ ጥየቃ ወደልጅቷ ቤት ይሄዱና በባህሉ መደረግ ያለበትን ሂደት ጨርሰው የሠርጉ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል።

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ሲከወን ከመተጫጨት እስከ ቅልቅል ባለው ሂደት የሚታዩ ትዕምርቶች ብሔረሰቡን የመግለጽ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በእያንዳንዱ ክዋኔ እንደዐውዱ የሚከናወኑ ክንውኖች የክዋኔን መዋቅር የተከተሉና በድግግሞሽ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመዱ ናቸው። በመሆኑም የት ቦታ ምን ማደረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ወቅት የሚለበሱ አልባሳት፣ የሚዜሙ ቃል ግጥሞች፣ የሚበሉና የሚጠጡ መጠጦችም እየተከናወነ ያለውን ሂደት የሚጠቁሙ እንጂ እንዲሁ ያለምክንያት የሚደረጉ እንዳልሆኑ ጥናቱ አመላክቷል። እንዲሁም የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ ሲከወን በውስጡ ሌሎች የፎክሎር ዘውጎችን መመልከቻ ዐውዶች እንዳሉ ለማየት ተችሏል። በመሆኑም በሀድያ ባህል ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ አጥኚዎች በጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት የሚታዩትን ሌሎች የፎክሎር ዘውጎች በመመርመር በማህበረሰቡ ዘንድ ለምን እንደሚከወኑና ምን ፋይዳ እንዳላቸው ቢፈትሹ ማህበረሰቡንና ባህሉን በሚገባ መረዳትና መግለጽ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ።

## ዋቢ ጽሑፎች


አለም እሸቱ። (1997)። *መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ*። አዲስ አበባ፡ ኮሜርሺያል ፕሪንቲንግ ኢንተርፕራይዝ።

አለባቸው ኬሚሶና ሳሙኤል ሀንዳሞ። (2002)። *የሀድያ ህዝብ ታሪክና ባህል*። አዲስ አበባ፡ ሰፈር አሳታሚ።

Bauman, Richard. (1983). "The Field Study of Folklore in Context" In *A Handbook of American Folklore*, Journal of American Folklore pp. 362-367. Dorson R(Ed).

………… Richard. (ed). (1992).Folklore, Cultural Performance and Popular Inrertainmenet,New York :Oxford Univeresity press.

Bell, Catherine. (1997). Ritual Theory, Ritual practice.New York:Oxford University press.

Ben-Amos, Dan (1993)."Context in Context" Theorizing Folklore towards New Perspective on the Politics of Culture, Western Folklore.vol.52, No.2/4.

Dorson, Richard.M. (ed). (1972). Folklore and Folk life: An introduction. chicago and London: the university of chicago press.

Goldstein, Kenneth S. (1964). *A Guide for Field Workes In Folklore.* Folklore Associates INC. Hatboro, Pennsylvania, USA.

Leslau, Wolf. (2007).Concise Amharic Dictionary.A.A:Shamma Books.

Mazama.Ama and Molefikete Asante. (ed).(2009). Encyclopidia of African Relgion. Sage Publications, Inc.

Sims Martha and Marthine, Stephens. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. United States of America: Utah University Press.

Solomon Mulugeta, (2008). *Socio Economic Base Line Survey of the Hadiya zone*. Childerens home society Family survices ethiopia:Rohobot printer.

Van Gennep, Arnold. (1960). The Rites of Passage. Trans. M. B. Visedom and G. L. Caffee. Chicago Press.